ደጀን ረታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

# ዘአሞጽ ነቢይ፡

## መቅድም

አሞጽ፡ ማለት፡ ጽኑዕ፡ በእግ
ዚአብሔር፤ አንድም፡ ጽኑዕ፡
እግዚአብሔር፤ አንድም፡ ጽንዓ፡
እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው፤

አማጽ፡ አዜቅ፡ እንዲል፤ አን
ድም፡ አሞስ፡ ይላል፤ ውዱድ፡
ማለት፡ ነው፤ አባቱ፡ ቴና፣
እናቱ፡ ሜስታ፡ ይባላሉ፣ ትው
ልዱ፡ ነገዱ ፡ ከነገደ፡ ስምዖን፡
ነው፤ ይህ፡ አርእስት፡ ነው፤
ሠለስቱ፡ ምዕት፡ ለመጻሕፍት፡
አርእስት፡ ሲሰጡ፡ አርእስት፡
ሰጥተውታል፤ እሱ፡ ግን፡
ነገሩን፡ ቃል፡ ዘኮነ፡ ብሎ፡
ያመጣል፣

### - ምዕራፍ ፩ -

፩፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡
ኀበ፡ አሞጽ፡ በአቃሪም፡ ዘቴቁሄ፣

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡
ነው፤ የቴቁሄ፡ አውራጃ፡ በም
ትሆን፡ በአቃሪም፡ ሳለ፡ ከአ
ሞጽ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡
የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡
ነው፤

ዘርእየ፡ በእንተ፡ እስራኤል፣

ሰዎች፡ እንዲማረኩ፤

ወበእንተ፡ ኢየሩሳሌም፣

አገሪቱ፡ እንድትጠፋ፡ አይቶ፡
የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤
አንድም፡ ዓሥሩ፡ ነገድ፡ ሁለቱ፡
ነገድ፡ እንዲማረኩ፡ አይቶ፡
የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤

በመዋዕለ፡ ያዝያን፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፣

በይሁዳ፡ ንጉሥ፡ በያዝያን፡
ዘመን፤

ወበመዋዕለ፡ ኢዮርብአም፡ ወልደ፡
ዮአስ፡ ንጉሠ፡ እስራኤል፣

በእስራኤል፡ በነገሠ፡ በዮአስ፡
ልጅ፡ በኢዮርብአም፡ ዘመን፡
የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፣
ስለምን፡ እነዚህን፡ አነሣቸው፡
ቢሉ፡ በነዚህ፡ ዘመን፡ ብመከ
ራቸው፡ ባስተምራቸው፡ አንሰ
ማም፡ ብለው፡ ተማረኩ፡
ለማለት፤

እምቅድመ፡ ፪ቱ፡ ዓመት፡ ዘድልቅልቅ፣

ዝብጥ፡ ፪ተ፡ አዕማደ፡ ጽጌያት፡
ወያድለቅልቁ፡ ዴዴያት፡ ካለው፡
ከሁለቱ፡ ዓመት፡ አስቀድሞ፡
እንዲህ፡ አለ፣



፪፤ ከመገዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡
እምጽዮን፡ ነበበ፡ ወእምኢየሩሳሌም፡
ወሀበ፡ ቃሎ፣

እግዚአብሔር፡ በነቢያት፡ በካ
ህናት፡ አድሮ፡ አናገረ፤ አንድም፡
ሰውሮ፡ አናገረ፣ የንጉሥ፡ ነገሩ፡
በዳበና፡ አዋጁ፡ በመዲና፡
እንዲሉ፤

ለሀዉ፡ መራዕየ፡ ኖሎት፣

እረኞች፡ ያሏቸው፡ መንጋዎች፡
ድርቅ፡ ሆኖባቸው፡ አለቀሱ፣
የሰዎችን፡ ለከብቶች፡ ሰጥቶ፡
ተናገረ፤ አንድም፡ ኖሎተ፡ መራ
እይ፡ ይላል፣ መንጋዎችን፡ የሚ
ጠብቁ፡ እረኞች፡ አለቀሱ፤ አን
ድም፡ ሕዝቡን፡ የሚሠሩ፡
የሚቀጡ፡ ነገሥታቱ፡ አዘኑ፤
አንድም፡ ነገሥታቱን፡ የሚመ
ክሩ፡ የሚያስተምሩ፡ መምህ
ራኑ፡ አዘኑ፣

አስመ፡ የብሰ፡ ርእሱ፡ ለቀርሜሎስ፣

ሥርዉ፡ ሲል፡ ነው፤ ሰክተት፡
እንዲል፡ ትግሬ፣ የዛፉ፡ ሥሩ፡
ደርቋልና፤ አንድም፡ የደጋው፡
ራስ፡ ምንጩ፡ ደርቋልና፤
አለቀሱ፤

፫፤ ወይቤ፡ እግዚአብሔር፡ በእንተ፡
ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለደማስቆ፣ ወበእንተ፡
አርባዕ፡ ኢይትመየጠሙ፤

ሦስትና፡ አራት፡ ሰባት፡ ይሆ
ናል፣ የደማስቆን፡ ሰዎች፡ ስለ
ፍጹም፡ ኃጢአታቸው፡ ይቅር፡
አልላቸውም፤ አንድም፡ ስለ፡
ነቅዓ፡ ሐልዮ፡ ስለቁርጥ፡
ሐልዮ፡ ስለ፡ ነቢቡ፡ ይቅር፡
እላቸዋለሁ፤

ወበእንተ፡ አርባዕ፣

ስለ፡ ገቢሩ፡ ግን፡ ይቅር፡ አል
ላቸውም፤ አንድም፡ ስለ፡ ጥቂቱ፡
ኃጢአታቸው፡ ይቅር፡ እላቸዋ
ለሁ፣ ስለብዙ፡ ኃጢአታቸው፡
ግን፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤
አንድም፡ ስለገደሉው፡ ኃጢአ
ታቸው፡ ይቅር፡ እላቸዋለሁ፣
ስለትርፉ፡ ግን፡ ይቅር፡ አልላ
ቸውም፤ አንድም፡ በሐልዮ፡
በነቢብ፡ በገቢር፡ በሠሩት፡
ኃጢአት፡ ንስሐ፡ ቢገቡ፡ ይቅር፡
እላቸዋለሁ፡ እኔን፡ ቢክዱ፡
ግን፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤

እስመ፡ ወሰርዎን፡ ለፅኑሳተ፡ ገለዓድ፣

በገለአድ፡ የፀነሱትን፡ ሴቶች፡
በመጋዝ፡ ሰንጥቀዋቸዋልና፡ ወን
ድን፡ ገደሉ፡ ሴትን፡ ገደሉ፡ ይሉ
ናል፡ ብለው፤ አንድም፡ አድገው፡
ጠላት፡ ይሆኑናል፡ ብለው፤

፬፤ ወእፌኑ፡ እሳተ፡ ላዕለ፡ ቤተ፡
አዛሄል፣

በአዛሄል፡ ወገኖች፡ ጦር፡ አመ
ጣባቸዋለሁ፣

ወትበልዕ፡ መሠረታቲሁ፡ ለወልደ፡
አዴር፣

የወልደ፡ አዴርን፡ ሥር፡ መሠ
ረቱን፡ ታጠፋለች፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፥ ወእቀጠቅጥ፡ መናሥግቲሃ፡ ለደማስቆ፤

የደማስቆን፡ ቁልፏን፡ እሰብረዋለሁ፤ አንድም፡ ኃያላኖቿን፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወእሤርዎሙ፡ ለሰብአ፡ አሞን፡ ኀበ፡ እሜትሮሙ፡ ለአሕዛብ፡ ሰብአ፡ ካራን፤

ወእሤርዎሙ፡ ለአሕዛብ፡ ሰብአ፡ ካራን፡ ኀበ፡ እሜትሮሙ፡ ለሰብአ፡ አሞን፡ ሲል፡ ነው፤ የአሞንን፡ ሰዎች፡ በማጠፋበት፡ መቅሠፍት፡ አሕዛብ፡ የሚሆኑ፡ የካራንን፡ ሰዎች፡ አጠፋቸዋለሁ፤ አንድም፡ እንዳለበት፡ ይሆናል፤ የካራን፡ ሰዎች፡ የሚሆኑ፡ አሕዛብን፡ ባጠፋሁበት፡ መዓት፡ መቅሠፍት፡ የአሞንን፡ ሰዎች፡ አጠፋቸዋለሁ፤ አሞን፡ ሌላ፡ አሞን፡ ናት፤

ወይፄወዉ፡ ቁረ፡ ሕዝቦሙ፡ ለሶርያ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ኃያላነ፡ ሕዝቦሙ፡ ኀሩያነ፡ ሕዝቦሙ፡ ሲል ነው፤ ቁርሎስ፡ ማለት፡ ኅሩይ፡ ማለት፡ እንደሆነ፡ እግዚአብሔር፡ ከሶርያ፡ ወገኖች፡ የተመረጡቱ፡ ይማረካሉ፡ አለ፤

፮፥ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ፡ ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለጋዛ፡ ወበእንተ፡ አርባዕ፡ ኢይትመየጦሙ፤

የጋዛን፡ ሰዎች፡ ስለ፡ ፍጹም፡ ኃጢአታቸው፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤ ትርጓሜው፡ እንዳለፈው፡ ነው፤

እስመ፡ ፄወዉ፡ (ዓፀዉ፡) ፄዋሁ፡ ለሰሎሞን፡ ከመ፡ ይዕፅውዎ፡ ውስተ፡ ኤዶምያስ፤

ሰሎሞን፡ ይማርካቸው፡ የነበሩ፡ አሕዛብ፤ አንድም፡ ሰሎሞን፡ አቀማጥሎ፡ ያኖራቸው፡ የነበሩ፡ እስራኤልን፡ በኤዶምያስ፡ ይዘንቸው፡ ዘንድ፡ ማርከዋቸዋልና፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤ ዓፀዉ፡ ማለት፡ ሲማርኳቸው፡ በሰንሰለት፡ ይዘዋቸው፡ ይሔዳሉ፤ ካገራቸው፡ ሲደርሱ፡ አሥረው፡ አምባ፡ ያግዟቸዋልና፤ አንድም፡ በፊት፡ አቅርበው፡ በኋላ፡ አርቀዋቸዋልና፤

፯፥ ወእፌኑ፡ እሳተ፡ ላዕለ፡ አረፍተ፡ ጋዛ፤

በሀገሪቱ፡ ድርቅ፡ በሰዎቹ፡ ጦር፡ አመጣባቸዋለሁ፤

ወትበልዕ፡ መሠረታቲሃ፤

ሥር፡ መሠረቷን፡ ታጠፋለች፤

፰፥ ወእሤርዎሙ፡ ለእለ፡ ይነብሩ፡ አዛጦን፤

በአዛጦን፡ የሚኖሩትን፡ ሰዎች፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወይጠፍዑ፡ አሕዛበ፡ አስቀሎና፤

የአስቀሎናም፡ ወገኖች፡ ይጠፋሉ፤

ወአመጽእ፡ እዴየ፡ ላዕለ፡ አቃሮን፤

በአቃሮን፡ ላይ፡ እደ፡ መዓቴን፡ አመጣለሁ፤



ወይጠፍዑ፡ ምስለ፡ አሕዛበ፡ ኢሎፍሊ፡ እለ፡ ተርፉ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ኢሎፍሊ፡ ያላት፡ ጌት፡ ናት፤ የቀሩቱ፡ ከጌት፡ ሰዎች፡ ጋር፡ ይጠፋሉ፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

፱፥ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ በእንተ፡ ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለጢሮስ፡ ወበእንተ፡ አርባዕ፡ ኢይትመየጦሙ፤

የጢሮስን፡ ሰዎች፡ ስለፍጹም፡ ኃጢአታቸው፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤

እስመ፡ ዓፀዉ፡ ፄዋሁ፡ ለሰሎሞን፡ ውስተ፡ ኤዶምያስ፤

ምርኮኛ፡ እንዲቀማጠል፡ ሰሎሞን፡ አቀማጥሎ፡ ያኖራቸው፡ የነበሩ፡ እስራኤልን፡ በኤዶምያስ፡ ዘግተዋልና፤

ወኢተዘከሩ፡ ኪዳነ፡ አበዊሆሙ፤

ዳዊት፡ ከኪራም፤ ኪራም፡ ከሰሎሞን፡ የተማማሉትን፡ መሐላ፡ አላሰቡምና፤

፲፥ ወእፌኑ፡ እሳተ፡ ላዕለ፡ ዐረፍተ፡ ጢሮስ፤

በሀገሪቱ፡ ድርቅ፡ በሰዎቹ፡ ጦር፡ አመጣለሁ፤

ወትበልዕ፡ መሠረታቲሃ፤

ሥር፡ መሠረቷን፡ ታጠፋለች፤

፲፩፥ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ በእንተ፡ ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለኤዶምያስ፡ ወበእንተ፡ አርባዕ፡ ኢይትመየጦሙ፤

የኤዶምያስን፡ ሰዎች፡ ስለፍጹም፡ ኃጢአታቸው፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤

እስመ፡ ዴገኖ፡ ለእኁሁ፤

ኤሳው፡ ወንድሙ፡ ያዕቆብን፡ ጦር፡ ይዞ፡ ተከትሎታልና፤

ወአርኰሰ፡ ማኅፀነ፡ ዲበ፡ ምድር፤

በማኅፀን ፡ የሚገኘውን፡ ፍቅር፡ አጥፍቷልና፤

ወበርበሮ፡ እንዘ፡ ይዛለፎ፡ ወያደነግፆ፤

እያዋተተ፡ ገንዘቡን፡ በዝብዞታልና፡ አስደንግጦታልና፤

ወዓቀበ፡ መራደ፡ በዘይመጽእ፤

በሚመጣበት፡ ጐዳና፡ ዘበኛ፡ አስቀምጦበታልና፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤

፲፪፥ ወእፌኑ፡ እሳተ፡ ላዕለ፡ ቴማን፤

በኤዶምያስ፡ በሀገሩ፡ ድርቅ፡ በሰዎቹ፡ ጦር፡ አመጣባቸዋለሁ፤

ወትበልዕ፡ መሠረታቲሃ፡ ለባሶር፤

ኤዶምያስን፡ ሥር፡ መሠረቷን፡ ታጠፋለች፤

፲፫፥ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ በእንተ፡ ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፤ ለደቂቀ፡ አሞን፡ ወበእንተ፡ አርባዕ፡ ኢይትመየጦሙ፤

እግዚአብሔር፡ የአሞንን፡ ልጆች፡ ስለፍጹም፡ ኃጢአታቸው፡ ይቅር፡ አልላቸውም፡ አለ፤

እስመ፡ አንቅዕዎን፡ ለፅኑሳተ፡ ገለአድ፤

በገለዓድ፡ የፀነሱትን፡ ሴቶች፡ ሰንጥቀዋቸዋልና፡ ትርጓሜው፡ እንዳለፈው፡ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአኪድዎ፡ ለእክሎሙ፡ ከመ፡ ያርኅቡ፡ ደወሎሙ፤

አገራቸውን፡ ያሰፉ፡ ዘንድ፡ እህ ላቸውን፡ አበራይተውታልና፤ አንድም፡ አገር፡ ያስርቡ፡ ዘንድ፤

፲፬፤ ወአነድድ፡ እሳተ፡ ላዕለ፡ ዐረ ፍተ፡ ራባ፤

በሀገሪቱ፡ ድርቅ፤ በሰዎቹ፡ ጦር፡ አመጣባቸዋለሁ፡ አለ፤

ወትበልዕ፡ መሠረታቲሃ፡ በውውአ፡ አመ፡ ዕለተ፡ ቀትል፤

ስልፍ፡ በሚደረግበት፡ ቀን፡ በድንፋታ፡ ሥር፡ መሠረቷን፡ ታጠፋለች፤

ወታድለቀልቅ፡ በዕለተ፡ ያኃልቅዋ፤

በሚያጠፉበት፡ ቀን፡ ትነዋወጣለች፤

፲፭፤ ወይፄውውዎሙ፡ ለነገሥ ቶሙ፡ ወለመኳንንቲሆሙ፡ ወለካህና ቲሆሙ፡ ኅቡረ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ነገሥታቱን፡ መኳንንቱን፡ ካህናቱን፡ ባንድ ነት፡ ይማርኳቸዋል፡ አለ።

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ በእንተ፡ ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለሞአብ፡ ወበእንተ፡ አርባዕ፡ ኢይትመየጦሙ፤

እግዚአብሔር፡ የሞአብን፡ ሰዎች፡ ስለፍጹም፡ ኃጢአታቸው፡ ይቅር፡ አልላቸውም፡ አለ፤

እስመ፡ አውዓዩ፡ አዕፅምቲሁ፡ ለን ጉሠ፡ ኤዶምያስ፡ ለግምስስ፤

የኤዶምያስን፡ ንጉሥ፡ ልጅ፡ ግምስስ፡ ለሚባል፡ ጣዖት፡ ሰውተዋልና፤ ወሠረፀ፡ አዕፅም ቲሆሙ፡ ለ፲ቱወ፪ቱ፡ ነገደ፡ እስ ራኤል፡ እንዲል፤ አንድም፡ አዕ ፅምቲሁ፡ ለዘይነግሥ፡ ሆኖንቴሁ፡ ሲል፡ ነው፤ ስለሱ፡ ፈንታ፡ የሚነግሠውን፡ ልጁን፡ ሰውተ ዋልና፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤

፪፤ ወእፌኑ፡ እሳተ፡ ላዕለ፡ ሞዓብ፤

በሀገሪቱ፡ ድርቅ፡ በሰዎቹ፡ ጦር፡ አመጣለሁ፤

ወትበልዕ፡ መሠረታተ፡ ዐረፋቲሃ፡ ወአውግሪሃ፤

ሥር፡ መሠረቷን፡ ከረብታ ዋን፡ ታጠፋለች፤

ወትመውት፡ ሞዓብ፡ በድካም፤

ሞዓብ፡ ሳብ፡ ሳብ፡ ብሏት፡ ትሞታለች፤

በውውዓ፡ ወበቃለ፡ ቀርን፤

በድንፋታ፡ በነጋሪት፡ ድምፅ፡ ትጠፋለች፤

፫፤ ወእሤርዎሙ፡ ለመኳንንቲሃ፡ ወለኵሎሙ፡ መላእክቲሃ፡ ምስሌሃ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ መኳንንቶቿን፡ አለቆቿን፡ ከሷ፡ ጋራ፡ አጠፋቸዋ ለሁ፡ አለ፤ መጽሐፍ፡ ትቶት፡ የሚሄደውን፡ በፊት፤ ይዞት፡



የሚሄደውን፡ በኋላ፡ ማምጣት፡ ልማዱ፡ ነው፤ በኦሪት፡ በፊት፡ የኤሳውን፤ በኋላ፡ የያዕቆብን፤ በሕፀጻን፡ በፊት፡ የይስማኤ ልን፤ በኋላ፡ የይስሐቅን ፡ እን ዳመጣ፡ ከዚህም፡ በፊት፡ የአ ሕዛብን፡ ተናግሮ፡ በኋላ፡ የእስ ራኤልን ፡ አመጣ፤

፬፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ በእንተ፡ ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለደቂቀ፡ ይሁዳ፡ ወበእንተ፡ አርባዕ፡ ኢይት መየጦሙ፤

እግዚአብሔር፡ ስለፍጹም፡ ኃጢ አታቸው፡ የይሁዳን፡ ልጆች፡ ይቅር፡ አልላቸውም፡ አለ፤

እስመ፡ ዓለዉ፡ ሕገ፡ እግዚአብሔር፤

ሕገ፡ እግዚአብሔርን፡ አፍር ሰዋልና፤

ወኢዓቀቡ፡ ትእዛዞ፤

ትእዛዙንም፡ አልጠበቁምና፤

ወአስሐቶሙ፡ ከንቶሆሙ፡ ዘገብሩ፡ አበዊሆሙ፤

አባቶቻቸው፡ የሠሩት፡ ጣዖት፡ አስቷቸዋልና፤

ወእሙንቱኒ፡ ተለዉ፡ ድኅሬሆሙ፤

እነሱም፡ ጣዖቱን፡ ተከትለዋ ልና፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤

፭፤ ወእፌኑ፡ እሳተ፡ ላዕለ፡ ቤተ፡ ይሁዳ፤

በይሁዳ፡ በሀገሪቱ፡ ድርቅ፡ በሰ ዎቹ፡ ጦር፡ አመጣባቸዋለሁ፤

ወትበልዕ፡ መሠረታቲሃ፡ ለኢየሩሳሌም፤

የኢየሩሳሌምን፡ ሥር፡ መሠ ረቷን፡ ታጠፋለች፤

፮፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ በእንተ፡ ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለእስራ ኤል፡ ወበእንተ፡ አርባዕ፡ ኢይትመ የጦሙ፤

እግዚአብሔር፡ እስራኤልን፡ ስለፍጹም፡ ኃጢአታቸው፡ ይቅር፡ አልላቸውም፡ አለ፤

እስመ፡ ሤጡ፡ ጻድቀ፡ በወርቅ፡ ወነ ዳየ፡ በአሣዕን፡ በዘይከይዱ፡ ምድረ፤

ጻድቅ፡ ነዳይ፡ ያለው፡ አንድ፡ ወገን፡ ነው፤ ድኃውን፡ በወርቅ፡ ምድር፡ በሚረገጡበት፡ ለጫማ፡ ሸጠውታልና፡ ማለት፡ ለጥቂት፡ ገንዘብ፡ ሸጠውታልና፤

፯፤ ወይኰርዑ፡ አርእስተ፡ ነዳያን፤

የድኆችን፡ ራስ፡ ይቀጠቅጣሉ፤

ወይመይጡ፡ ፍትሐ፡ ምስኪናን፤

የድሆችን፡ ፍርድ፡ ይለውጣሉ፤ አንድም፡ እስመ፡ ሤጡ፡ ጻድቀ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ጻድቅ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔርን፡ ለጥቂት፡ ገን ዘብ፡ ሸጠዋልና፤ ማለት፡ በጫማ፡ ዋጋ፡ ሸጠዋልና፤ ሠላሳ ብር፡ እንደ፡ አምላክነቱ፡ የጫማ፡ ዋጋ፡ ነውና፤ የሐዋርያትን፡ ራስ፡ ይቀ ጠቅጣሉ፤ የድሆችንም፡ ፍርድ፡ ይለውጣሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

አብ: ወወልድ: ያብውእ: ውስተ: አሐቲ: ብእሲት: ከመ: ያርኵሱ: ሕገ: አምላኮሙ፤

የፈጣሪያቸውን: ሕግ: ያስነ ቅፉ: ዘንድ: አባትና: ልጅ: ከአንዲት: ሴት: ይደርሳሉ፤

፰፤ ወየዓሥሩ: አልባሲሆሙ: ወይ ገብሩ: መንጦላዕተ: ዲበ: ምሥዋዕ፤

ልብሳቸውን: መጋረጃ: አድር ገው: ምሥዋዓ: ጣዖቱን: ይጋርዳሉ፤

ወይሰትዩ: ወይነ: ትዕግልት: በቤተ: አምላኮሙ፤

ቀምተው: ያመጡትን: ወይኑን: በጣዖቱ: ቤት: ይጠጣሉ፤ አን ድም: ለጣዖቱ: የሚያቀርቡ ትን : ወይነ: ትዕግልት: አለው፤

፱፤ አንሰ: አጥፋዕክዎ: ለአሞሬ ዎን: እምቅድሜክሙ: ዘኑኁ: ከመ: ኑኁ: አርዝ: ወጽንዑ: ከመ: ጽንዓ: አውልዕ፤

ጽናቱ: እንደወይራ: ገናንነቱ: እንደ: ደጋ: ዛፍ: የሚሆን: አሞ ሬዎንን: ከፊታችሁ: አጠፋሁት፤

ወአጥፋዕኩ: ፍሬሁ: እምላዕሉሁ፤

ከሉ: ለይቼ፤ አንድም: ከሉ: የተ ወለደውን: ልጁን: አጠፋሁ፤

ወሥረዊሁ: በታሕቴሁ፤

ከሉ: በታች: የሚሆን: የልጅ: ልጁን: አጠፋሁ፤ አንድም: አባ ትነቱን: አጠፋሁ፤

፲፤ ወአነ: አውጻዕኩክሙ: እም ድረ: ግብፅ፤

እኔ: ከግብፅ: አወጣኋችሁ፤

ወወሰድኩክሙ: ገዳመ: አርብዓ: ዓመተ: ከመ: አውርስክሙ: ምድረ: አሞሬዎን፤

የአሞሬዎንን: አገር: አወርሳ ችሁ: ዘንድ: አርባ: ዘመን: በም ድረ: በዳ: አዞርኋችሁ፤ አንድም: የአሞሬዎንን: አገር: አወርሳ ችሁ: ዘንድ: አስቀድሜ: አሕ ዛብን: አጠፋሁት፤

፲፩፤ ወነሣእኩ: እምደቂቅክሙ: ነቢያተ፤

ከልጆቻችሁ: ነቢያትን: አሥነሣሁ፤

ወእምወራዙቲክሙ: እለ: ይቄድሱ: ሲተ፤

ከጐልማሶችም: ቀድስ: ሲተ: ሌዋውያን: ብዬ: ካህናቱን: አስነሣሁ፤

ኢኮነሁ: ከመዝ: ኦ: ደቂቀ: እስራኤል: ይቤ: እግዚአብሔር፤

የእስራኤል: ልጆች: እንዲሁ: አላደረጉህምን: አለ: እግዚ አብሔር፤

፲፪፤ ወታስትይዎሙ: ወይነ: ለቅዱሳንየ፤

ሊመክሯችሁ: ሊያስተምሯችሁ: ቢመጡ: ነቢያት: ካህናትን: የመጣችሁበትን: በልታችሁ: ጠጥታችሁ: ሂዱ: ብላችሁ: ታ[illegible]ችሁ፤



ወትከልዕዎሙ: ለነቢያት፤

እንዳያስተምሯችሁ: ነቢያትን: ትከለክሏቸዋላችሁ፤

ወትብልዎሙ: ኢትትነበዩ: ለነ፤

ከመዝ: ይቤ: እግዚአብሔር: ብላ ችሁ፤ አትንገሩን: ትሏቸዋላችሁ፤

፲፫፤ በእንተ: ዝንቱ: አነ: አንከ ረኵረክሙ: በታሕቴክሙ: ከመ: ያን ኰረኵር: ሠረገላ: ብርዓ፤

ሠረገላ: ከበታቹ: ያለውን: ገለባ: እንዲያደቅ: ስለዚህ: ነገር: አጠፋችኋለሁ፤

፲፬፤ ወኢይክል: ረዋጺ: አምሥጠ፤

እንደ: አዛሄል: ያለ: ነው፤ ከጦሩ: ማምለጥ: አይቻለውም፤

ወኃያልኒ: ኢይእኅዝ: በጽንዑ፤

እንደ: ኢዮአብ: ያለው: በኃ ይሉ: መያዝ: አይቻለውም፤

ወመሥተቃትልኒ: ኢያድኅን: ነፍሶ፤

እንደ: አቢሳ: ያለው: አርበኛም: ሰውነቱን: ማዳን: አይቻለውም፤

፲፭፤ ወነዳፊኒ: ኢይቀውም፤

እንደ: ዮናታን: ያለ: አርበኛ: አይጸናም፤

ወረዋጺኒ: ኢያመሥጥ፤

እንደ: ኢያቡስቴ: ያለ: ፈጣኑም: አያመልጥም፤

ወመስተቃትልኒ: ኢያወጽእ: ነፍሶ፤

እንደ: ኤልያናን: ያለ: አርበኛ: ሰውነቱን: አያድንም፤

፲፮፤ ወኃያልኒ፤

እንደ: አዲኖን: ያለ: አርበኛ: አይድንም፤

ዘቦ: ልብ: ኢይቀውም: በዕለተ: ቀትል፤

አእምሮ: ያለው: አርበኛውም: በሰልፍ: ቀን: አይቆምም፤

አላ: እራቆ: ይጐይይ: ይእተ: አሚረ: ይቤ: እግዚአብሔር፤

ጋሻውን: ጦሩን: ጥሎ: ይሸ ሻል: እንጂ: ያን: ጊዜ: እግዚ አብሔር: እንዲህ: አለ።

## ምዕራፍ ፫

፩፤ ስምዑ: ዘንተ: ነገረ: ዘይቤ ለክሙ: እግዚአብሔር: ቤተ: እስራኤል፤

የእስራኤል: ወገኖች: እግዚአ ብሔር: የተናገረውን: ነገር: ስሙ፤

ወኵሉ: ሕዝብ: ዘአውጽአክሙ: እም ድረ: ግብፅ፤

ከግብፅ: ያወጣችሁ: ወገኖቼ: ሁሉ: ስሙ፤

፪፤ እንዘ: ይብል: ዳዕሙ: አዕ መርኩ: እምኵሉ: አሕዛበ: ምድር፤

በዚህ: ዓለም: ካሉ: አሕዛብ: ሁሉ: እናንተን: ብቻ: ወደድሁ: ብዬ: እንዳወጣኋችሁ: ስሙ፤

በእንተ: ዝንቱ: እትቤቀለክሙ: በእ ንተ: ኵሉ: ኃጢአትክሙ፤

ስለዚህ: ነገር: በኃጢአታችሁ: ምክንያት: አጠፋችኋለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይወድቅ፡ ውስተ፡ ምድር፤

ተሰብሮ፡ በምድር፡ ላይ፡ ይወድቃል፤

፲፭፤ ወእቀትሎሙ፡ ለቤተ፡ ምክራም፡ ወለቤተ፡ ሐጋይ፤

እነሥቶሙ፡ ሲል፡ ነው፤ ቀተለና፡ ነሥተ፡ ይወራረሳሉ፤ ንሥትዎ፡ ለዝንቱ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ አለ፤ ቅትልዎ፡ ሲል፡ ክረምት፡ የሚከርሙባቸውን፡ በጋ፡ የሚገቡባቸውን፡ አፈርሳቸዋለሁ፡ አለ፤ ቤተ፡ ምክራም፡ የሚለው፡ ክረምት፡ ከቆላ፤ በጋ፡ ከደጋ፡ ይከርማሉና፤ አንድም፡ ክረምት፡ ከምድር፡ ቤት፡ ይቀመጣሉ፤ በበጋ፡ በሰገነት፡ ይባጃሉና፡ እንዲህ፡ አለ፤

ወይትኀጐላ፡ አብያት፡ ዘቀርነ፡ ነጌ፤

በዝሆን፡ ጥርስ፡ የተሠሩ፡ ቤቶች፡ ይጠፋሉ፤ አክዓብ፡ በሰማርያ፡ በዝሆን፡ ጥርስ፡ ቤት፡ ሠርቶ፡ ነበርና፤

ወይትዌሰኩ፡ አብያት፡ ካልዓን፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ሌሎችም፡ ቤቶች፡ ይጠፋሉ፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤ አንድም፡ ዘቀርነ፡ ነጌ፤ የባለፀጎች፡ ቤት፡ ወይትዌሰኩ፡ አብያት፡ ካልዓን፡ በጭቃ፡ በኖራ፡ የተሠሩ፡ ሌሎች፡ ቤቶችም፡ አብያተ፡ ካልዓን፡ ይላል፡ የድሆችም፡ ቤቶች፡ ይጠፋሉ።

# ምዕራፍ ፬

፩፤ ስምዑ፡ ዘንተ፡ ነገረ፡ ዕጐልተ፡ ባሳን፡ እለ፡ ውስተ፡ አድባረ፡ ሰማርያ፤

በሰማርያ፡ የሚኖሩ፡ የሴቶችን፡ ጉድ፡ ስሙ፤

እለ፡ ይትዔገላ፡ ነዳየ፡ ወይከይዳ፡ ምስኪነ፤

ድኃውን፡ የሚቀሙ፡ ምስኪኑን፡ የሚረግጡ፤

እለ፡ ይብላሆሙ፡ ለአጋዕዝቲሆሙ፡ ሀቡነ፡ ንስተይ፡ ወንሰተይ፤

ባሎቻቸውን፡ እንዲህ፡ የሚሏቸው፡ የድኃውን፡ ገንዘብ፡ ቀምታችሁ፡ ስጡን፡ እንብላ፡ እንጠጣ፡ የሚሉ፡ የሴቶችን፡ ጉድ፡ ስሙ፤

፪፤ መሐለ፡ እግዚአብሔር፡ በርእሱ፤

እግዚአብሔር፡ ሕያውየ፡ አማንየ፡ በርእስየ፡ ብሎ፡ በራሱ፡ ማለ፤

ናሁ፡ ይመጽእ፡ መዋዕል፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እነሆ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ወራት፡ ይመጣል፡ አለ፤

ወይነሥኡክሙ፡ በንዋየ፡ ሐቅሎሙ፤

ጋሻ፡ ጦራቸውን፡ ይዘው፡ ማርከው፡ ይወስዷቸዋል፤

ወእለሂ፡ እምኔክሙ፡ ያበስሉክሙ፡ በጽሕርት፡ እኩያን፡ ወጽልጐዋን፤

ከናንተ፡ ወገን፡ ከዳተኞች፡ ክፉዎች፡ የሆኑ፡ ሰዎች፡ በድስት፡



ይቀቅሏችኋል፡ ማለት፡ ጽኑዕ፡ መከራ፡ ያመጡባችኋል፤

፫፤ ወያወጽኡክሙ፡ ዕራቃኒክሙ፤

ራቁታችሁን፡ ማርከው፡ ይወስዷችኋል፤

ወትትናጸሩ፡ በበይናቲክሙ፤

እርስ፡ በርሳችሁ፡ ትተያያላችሁ፤ አንድም፡ ወንዱ፡ የሴቲቱን፡ አካል፡ ያያል፤ ሴቲቱም፡ የወንዱን፡ አካል፡ ታያለች፤ ትትናገሩ፡ ቢል፡ ትወዛገባላችሁ፤ አንተ፡ ጣዖት፡ አምልክ፡ ብለኸኝ፤ አንቺ፡ ጣዖት፡ አምልክ፡ ብለሺኝ፡ ብለው፡ ይወዛገባሉና፤

ወእገድፈክሙ፡ ውስተ፡ ደብረ፡ ሬማ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ እግዚእ፤

ሬማ፡ ጽኑ፡ ገደል፡ ነው፤ እግዚአብሔር፡ በጽኑ፡ መከራ፡ እጥላችኋለሁ አለ፤

፬፤ ቦእክሙ፡ ቤቴል፡ ወአበስክሙ፤

ከቤተ፡ ጣዖት፡ ገብታችሁ፡ በደላችሁ፤

ወበገልገላሂ፡ አብዛኀክሙ፡ ኃጢአተክሙ፤

በገልገላም፡ ኃጢአታችሁን፡ አብዝታችሁ፡ ሠራችሁ፤

ወአምጻእክሙ፡ መሥዋዕተክሙ፡ በጽባሕ፤

መሥዋዕታችሁንም፡ ፈጥናችሁ፡ ወደቤተ፡ ጣዖት፡ አመጣችሁ፤

ወእስከ፡ ሠሉስ፡ ዕለት፡ አሥራቲክሙ፤

እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ ማለት፡ አሥራቱን፡ ፈጥናችሁ፡ አመጣችሁ፤

ወአጠንክሙ፡ በአፍኣ፤

ዕጣኑን፡ በአፍኣ፡ ለጣዖቱ፡ አጠናችሁ፤

፭፤ ወሰመይክምዎ፡ መሥዋዕተ፡ ፈቃድ፤

የጣዖቱን፡ መሥዋዕት፡ መሥዋዕተ፡ ፈቃድ፡ አላችሁት፤

ንግሩ፡ ዘአፍቀሩ፡ ደቂቀ፡ እስራኤል፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ እግዚእ፤

ጌታችን፡ እግዚአብሔር፡ እስራኤል፡ የወደዱትን፡ ንገሩ፡ አለ፤

፮፤ ወአነ፡ እሁበክሙ፡ ትዕርሰ፡ ስነኒክሙ፡ በኵሉ፡ ፍናዊክሙ፤

በጕዳናችሁ፡ ሁሉ፡ ጥርስ፡ ጥርሳችሁን፡ እያሉ፡ እንዲወስዷችሁ፡ አደርጋለሁ፤

ወረኀበ፡ እክል፡ በኵሉ፡ በሐውርቲክሙ፤

አመጽእ፡ ያለበት፡ ነው፤ በሀገራችሁ፡ ሁሉ፡ ቀጠና፡ አመጣለሁ፡ አለ፤

ወኢተመየጥክሙ፡ ኀቤየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ በአምልኮት፡ ወደኔ፡ አልተመለሳችሁም፡ አለ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወአነ፡ ከላእኩክሙ፡ ዝናመ፡ እምቅድመ፡ ፫ቱ፡ አውራኅ፡ ዘማዕረር፤

ከኅዳር፡ ከታኅሣሥ፡ አስቀድሞ፡ የሚሆን፡ የሐምሌን፡ የነሐሴን፡ ዝናም፡ ነሣኋችሁ፤ አንድም፡ ለዝናምም፡ ቅሉ፡ መከር፡ አለው፡ ብሎ፡ ከነሐሴ፡ ከሐምሌ፡ ከሰኔ፡ አስቀድሞ፡ የሚሆን፡ የሚያዝያን፡ የግንቦትን፡ ዝናም፡ ነሣኋችሁ፤

ወአዘንም፡ ውስተ፡ አሐቲ፡ ሀገር፡ ወውስተ፡ ካልዕታ፡ ሀገር፡ ኢያዘንም፤

በአንዲቱ፡ ሀገር፡ አዘንማለሁ፤ በሁለተኛይቱ፡ ሀገር፡ አላዘንምም፤ ይኸውም፡ የጌታ፡ መዓቱም፡ ምሕረቱም፡ ነው፤

ወኅበ፡ ኢይዘንም፡ ... ይየብስ፤

ዝናም፡ የማይዘንብበት፡ ይደርቃል፤

፰፤ ወይትጋብኡ፡ ብዙኃት፡ አህጉር፡ ውስተ፡ አሐቲ፡ ሀገር፡ ይስተዩ፡ ማየ፡ ወኢይረውዩ፤

ውሀውን፡ ይጠጡ፡ ዘንድ፡ ብዙ፡ ሀገሮች፡ ወደ፡ አንዲት፡ ሀገር፡ ይሰበሰባሉ፤ አንድም፡ ብዙ፡ ሀገሮች፡ ውሀውን፡ ይጠጣሉ፤ አይረኩም፤ አንድም፡ ወአዘንም፡ ውስተ፡ አሐቲ፡ ሀገር፡ ብለህ፡ መልስ፤ ነቢያትን፡ በአንዲት፡ ሀገር፡ እንዲያስተምሩ፡ አደርጋቸዋለሁ፤ በሁለተኛዪቱ፡ ሀገር፡ እንዳያስተምሩ፡ አደርጋቸዋለሁ፤

ወምስለ፡ ከመዝ፡ ኢተመየጥክሙ፡ ኀቤየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ከዚህም፡ ጋራ፡ በአምልኮት፡ ወደኔ፡ አልተመለሳችሁም፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

፱፤ ወአነ፡ ቀሠፍኩክሙ በፈፀንት፡ ወበብድብድ፤

እኔም፡ በፌራ፡ በቸነፈር፡ አጠፋኋችሁ፤

ወሰሚሮ፡ አቅማኒክሙ፡ ወወይንክሙ፡ ወበለስክሙ፡ ወዘይትክሙ፡ በልዖ፡ አናኲዕ፤

ተክላችሁ፡ ወይኑ፡ በለሱ፡ ዘይቱ፡ አምሮ፡ ሠምሮ፡ ሳለ፡ ኩብኩባ፡ በላው፡ ማለት፡ ናቡከደነፆር፡ አጠፋው፤

ወምስለ፡ ከመዝ፡ ኢተመየጥክሙ፡ ኀቤየ፤ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ከዚህም፡ ጋር፡ ወደኔ፡ አልተመለሳችሁም፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

፲፤ ወፈነውኩ፡ ላዕሌክሙ፡ ሞተ፡ ግብጽ፤

የድንገት፡ ሞት፡ አመጣሁባችሁ፤ አንድም፡ ሞተ፡ ግብፅ፡ ይላል፤ ሞተ፡ በኵር፡ አመጣሁባችሁ፤



ወቀተልክምሙ፡ በኲናት፡ ለወራዙቲክሙ፤

ልጆቻችሁን፡ በጦር፡ አጠፋኋቸው፤

ወማኅረኩ፡ አፍራሲክሙ፤

ፈረሶቻችሁ፡ እንዲማረኩ፡ አደርጋለሁ፤

ወአምጻእኩ፡ እሳተ፡ ላዕለ፡ ተዓይኒክሙ፡ ወቀሠፍኩክሙ፤

በሠራዊቶቻችሁም፡ ጦር፡ አምጥቼ፡ አጠፋኋቸው፤

ወበዝኒ፡ ኢተመየጥክሙ፡ ኀቤየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

በዚህም፡ ወደኔ፡ አልተመለሳችሁም፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

፲፩፤ ገፍታዕኩክሙሂ፡ በከመ፡ ገፍታዕክዎሙ፡ ቅድመ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰዶም፡ ወለገሞራ፤

አስቀድሜ፡ ሰዶም፡ ገሞራን፡ እንዳጠፋኋቸው፤ አጠፋኋችሁ፤ አንድም፡ እንደ፡ እሣ፡ መቅሎ፡ እንደቆላኋቸው፡ እንደሰዶም፡ እንደ፡ ገሞራ፡ አጠፋኋችሁ፤

ወኮንክሙ፡ ከመ፡ ትንታግ፡ እሳት፡ ዘአውጽእዎ፡ እምእፍሐም፤

ከፍም፡ ለይቶ፡ እንዳወጡት፡ እንደእሳት፡ ትንታግ፡ ሆናችሁ፤ ያ፡ ጥቂት፡ እንደሆነ፡ ጥቂት፡ ቀራችሁ፤

ወበዝኒ፡ ኢተመየጥክሙ፡ ኀቤየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

በዚህም፡ በአምልኮት፡ ወደኔ፡ አልተመለሳችሁም፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

፲፪፤ በእንተ፡ ዝንቱኬ፡ ከመዝ፡ እሬስየከ፡ እስራኤል፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ እስራኤል፡ ለዔዋዌ፡ ሳድርግህ፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤

እስመ፡ ከመዝ፡ ዘእሬስየከ፤

እስራኤል፡ የማደርግህስ፡ እንዲህ፡ ነው፤

ትደሎ፡ ከመ፡ ትጸውዕ፡ ስመ፡ አምላክከ፤

የፈጣሪህን፡ ስም፡ ትጠራ፡ ዘንድ፡ እንድትዘጋጅ፡ አደርግሃለሁ፤

፲፫፤ እስመ፡ አነ፡ ውእቱ፡ ዘአጸንዕ፡ ነጐድጓደ፤

ነጐድጓድን፡ የፈጠርሁ፡ እኔ፡ ነኝ፤

ወእፈጥር፡ መ...ፈሰ፤

ነፋስን፡ የፈጠርሁ፡ እኔ፡ ነኝ፤ አንድም፡ ደም፡ የማረጋ፡ እኔ፡ ነኝ፤

ወእፈጥር፡ መንፈሰ፡ ለብእሲ፤

እውቀትን፡ በሰው፡ የማሳድር፡ እኔ፡ ነኝ፤ አንድም፡ ሥጋን፡ የፈጠርሁ፡ እኔ፡ ነኝ፤ ነፍስንም፡ የማዋሕድ፡ እኔ፡ ነኝ፤ አንድም፡ ነቢያትን፡ ይወርዳል፡ ይወለዳል፡ ብለው፡ እንዲያስተምሩ፡ የማደርግ፡ እኔ፡ ነኝ፤ ከዚያ፡ አስቀድሞ፡ መንፈስ፡ ረድኤትን፡ ያሳደርሁባቸው፡ እኔ፡ ነኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

ከመ: ይዜንዉ: በእንተ: መሚሁ: ዘይ
ገብር: በጽባሕ፤

ፈጥኖ: ሚጠትን: የሚያደርግ:
የዘሩባቤልን: ነገር: ለእስራኤል:
ይነግሩ: ዘንድ።

ወይትሌዓል: ውስተ: ኑኃ: ለምድር፤

ከባቢሎን: ሩቅ: ወደሆነች: ወደ:
ኢየሩሳሌም: ትሩፋንን: ይዞ:
የሚወጣ: የዘሩባቤልን: ነገር:
ይናገሩ: ዘንድ። አንድም: ዘአ
ጸንዕ: ነጐድጓደ: ብለህ: መልስ፤
ሐዋርያት: ወረደ: ተወለደ:
ብለው: እንዲያስተምሩ: ያደ
ረግሁ: እኔ: ነኝ፤ መንፈስ:
ቅዱስን: በሐዋርያት: ያሳደርሁ:
እኔ: ነኝ፤ ፈጥኖ: ሚጠተ: ነፍ
ስን: የሚያደርግ: የክርስቶስን:
ነገር: ያስተምሩ: ዘንድ: በሰባት:
ክንድ: መስቀል: የተሰቀለ።

እግዚአብሔር: እግዚእ: ዘኵሉ: ይመ
ልክ: ስሙ፤

ይህን: ሁሉ: የሚያደርግ: ሁሉን:
የሚገዛ: እግዚአብሔር: ነው።

## ምዕራፍ ፭

፩፤ ስምዑ: ቃለ: እግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔርን: ነገር: ስሙ።

ዘአወጽእ: ለክሙ: ሰቆቃወ: ቤተ:
እስራኤል፤

የእስራኤል: ወገኖች: ለናንተ:
የማወጣውን: ሙሾ: ስሙ።

፪፤ ወድቀት: ወኢተንሥአት: እንከ:
ድንግለ: እስራኤል፤

ድልድል: ቅምጥል: ቤተ: እስ
ራኤል: በመከራ: ወደቀች:
በረድኤት: አልተነሣችም።

ድኅፀት: በውስተ: ምድራ: ወኃጥአት:
ዘያነሥኣ፤

በሀገሯ: ሳለች: በመከራ: ተሰ
ነካከለች: በረድኤት: የሚያነ
ሣት: አጣች።

፫፤ እስመ: ከመዝ: ይቤ: እግ
ዚአብሔር፤

እግዚአብሔር: እንዲህ: ብሏልና።

ሀገር: እንተ: እምውስቴታ: ይወጽኡ:
፲፻ት: ይተርፉ: ፻ት፤

ሺህ: ሰዎች: የሚወጡባት:
አገር: ዘጠኙ: መቶ: ሙተው:
አልቀው: መቶው: ይቀራሉ።

ወእንተ: እምኔሃ: ይወጽኡ: ፻ት:
ይተርፉ: ፲ቱ: ለቤተ: እስራኤል፤

መቶ: ሰዎች: የሚወጡባት:
አገር: ዘጠናው: አልቀው: አሥር:
ሰዎች: ለቤተ: እስራኤል: ይቀ
ራሉ። አንድም: ዘጠናው: ሰዎች:
ሙተው: አሥር: ሰዎች: ይቀ
ራሉ፤ ብሏልና: አሥር: ሰዎች:
ይቀራሉ።

፬፤ እስመ: ከመዝ: ይቤ: እግዚአ
ብሔር: ለቤተ: እስራኤል፤

እግዚአብሔር: ቤተ: እስራኤ
ልን: እንዲህ: ብሏልና።



ኅሡኒ: ወተሐይዉ፤

በአምልኮት: ፈልጉኝ: ከመከራ:
ትድናላችሁ።

፭፤ ወኢትኅሥሡ: ቤቴል፤

ወደቤተ: ጣዖት: መሄድን:
አትውደዱ።

ወኢትሑሩ: ገልገላኒ፤

ጣዖት: ለማምለክ: ወደገልገላም:
አትሂዱ።

ወኢትዕርጉ: ኀበ: አዘቅተ: መሐላ፤

ወደቤርሳቤህም: አትውጡ።

እስመ: ገልገላኒ: ተገልግሎ: ትትገለገል፤

ተዜውዎ: ትዜወው: ሰስሎ:
ትሴስል: ሲል: ነው። ገልገላ:
ፈጽማ: ትጠፋለችና።

ወቤቴልኒ: ትኩውን: ከመ: ዘኢሀለወት፤

ቤቴልም: እንዳልነበረች:
ትሆናለችና።

፮፤ ኅሥዎ: ለእግዚአብሔር:
ወተሐይዉ፤

እግዚአብሔርን: በአምልኮት:
ፈልጉት: ከመከራው: ትድ
ናላችሁ።

ከመ: ኢትንድዱ: በእሳት: ቤተ: ዮሴፍ፤

የዮሴፍ: ወገኖች: በመዓት:
እንዳትጠፉ።

ወትበልዖሙ: መዓት፤

መዓት: መቅሠፍት: ታጠፋ
ቸዋለች።

ወየኀጥዖ: ዘያጠፍዕ: ሎሙ: እሳ
ቶሙ: ለቤተ: እስራኤል፤

የእስራኤል: ወገኖች: መዓ
ቱን: መቅሠፍቱን: የሚያርቅ
ላቸው: አጡ፤ መዓት: መቅ
ሠፍት: በብዙ: ወገን: ይመስ
ሳል፤ እንደሙሴ: ያለ: ነቢይ:
የተገኘ: እንደሆነ: መቅሠ
ፍት: ይመስሳል። እምትጥ
ስዮሙ: ለእሉ: ሕዝብ: ጠስ
የኒ: ብሎ: መዓቱን: መቅሠ
ፍቱን: እንደመለሰ፤ እንደ:
ኢያሱ: ያለ: መስፍን: የተገኘ:
እንደሆነ: መዓት: መቅሠፍት:
ይመስሳል።

ለምንት: አዕድዎ: አዕደውኮ:
ለገብርከ: ወናሁ: እስራኤል:
ሜጠ: ዘባኖ: ቅድመ: ፀሩ፤
ብሎ: መዓቱን: እንደመለሰ፤
እንደ: ዳዊት: ያለ: ንጉሥ:
የተገኘ: እንደሆነ: መዓት:
መቅሠፍት: ይመስሳል።

ምንተ: ገብሩ: እሉ: አባግዕ:
አነ: ኖላዊሆሙ: ዘአበስኩ:
ብሎ: መዓቱን: መቅሠፍቱን:
እንደመለሰ፤ እንደ: ሕዝቅያስ:
ያለ: ንጉሥ: የተገኘ: እንደ
ሆነ: መዓት: መቅሠፍት: ይመ
ስሳል፤ ርኢ: ትእይርቶ: ለሰ

www.ethiopianorthodox.org

ናክሬም፡ ብሎ፡ መዓቱን፡ እንደ መለሰ፤ እንደ፡ ሰብአ፡ ነነዌ፡ ንስሐ፡ ገብተው፡ መዓቱን፡ እንደመለሱ፤

፯፤ እግዚአብሔር፡ ዘይነብር፡ ውስተ፡ ሰማይ፤

በሰማይ፡የሚኖር፡እግዚአብሔር፤

ወያፀምዕ፡ ፍትሐ፡ ውስተ፡ ምድር፤

በዚህ፡ ዓለም፡ የሰውን፡ ሁሉ፡ ጸሎት፡ የሚሰማ፤

፰፤ ዘይገብር፡ ኮሎ፡ ወያስተራትዕ፤

ይህን፡ ሁሉ፡ የሚያደርግ፡ እሱ፡ ነው፤ ዘይገብር፡ ኮሎ፡ ባለው፡ ኬማ፡ ሴኬላ፡ የሚል፡ አብነት፡ ይገኛል፤ ጃጀታ፡ ድግኸግኸታ፡ ማለት፡ ነው፤ ሁሉን፡ የሚያ ቀና፡ እሱ፡ ነው፤

ወይመይጦ፡ ለብርሃን፡ መንገለ፡ መስዕ፤

ፀሐይን፡ ወደ፡ ምሥራቅ፡ የሚ መልሰው፡ እሱ፡ ነው፤

ወያጸልም፡ መዓልተ፡ ከመ፡ ሌሊት፤

ተድላውን፡ ደስታውን፡ በመከራ፡ የሚለውጥ፡ እሱ፡ ነው፤

ዘይጼውዖ፡ ለማየ፡ ባሕር፡ ወይክዕዎ፡ ውስተ፡ ገጸ፡ ምድር፤

ውቅያኖስን፡ በደመና፡ ቋጥሮ፡ የሚያመጣው፡ እሱ፡ ነው፤ በዚህ፡ ዓለም፡ የሚያዘንመው፡ እሱ፡ ነው፤ አንድም፡ ዘይጼውዖ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ስልምናሶርን፡ ከፋርስ፡ የጠራው፡ በኢየሩሳ ሌም፡ ያሰፈረው፡ እሱ፡ ነው፤

እግዚአብሔር፡ዘኮሎ፡ይመልክ፡ስሙ፤

ይኸን፡ ሁሉ፡ ያደረገ፡ እግዚአ ብሔር፡ ስሙ፡ ዘኮሎ፡ ይመ ልክ፡ ነው፤

፱፤ ዘያነሥእ፡ ቅጥቃጤ፡ ላዕለ፡ ኃያላን፤

በኃያላኑ፡ መከራ፡ የሚያመጣ ባቸው፡ እሱ፡ ነው፤

ወኃሣረ፡ ያመጽእ፡ ላዕለ፡ አጽዋን፤

በአምባዎች፡ መሰበርን፡ የሚ ያመጣባቸው፡ እሱ፡ ነው፤ አን ድም፡ በአርበኛው፡ ተዋርዶን፡ የሚያመጣ፡ እሱ፡ ነው፤

፲፤ እምኖኅት፡ ፀልዑ፡ ዘይጌ ሥጾሙ፤

የሚመክራቸው፡ የሚያስተምራ ቸው፡ ነቢዩን፡ ከደጅ፡ (ከዓደባባይ) ጣሉት፤ ሲመክሯቸው፡ ሲያ ስተምሯቸው፡ የሄዱ፡ እንደ ሆነ፡ የመጣችሁበትን፡ በልታ ችሁ፡ ጠጥታችሁ፡ ሂዱ፡ እንጂ፡ ትምህርት፡ ለምናችን፡ ይሏቸ ዋልና፤

ወአስቈረሩ፡ ቃለ፡ ጽድቅ፤

እውነተኛውን፡ ሕግ፡ ችላ፡ አሉ፤

፲፩፤ ወይከርዑ፡ አርእስተ፡ ነዳያን፤

የድሆችን፡ ራስ፡ ይቀጠቅጣሉ፡



ወነሣእክሙ፡ ሕልያነ፡ በኀቤሆሙ፤

ቦሙ፡ ሲል፡ ነው፤ መማለጃ፡ ተቀበላችሁባቸው፤

ወኃረይክሙ፡ አብያተ፡ ሠናያተ፡ ትሕንፁ፤

ጌጠኛ፡ ቤት፡ ትሠሩ፡ ዘንድ፡ ወደዳችሁ፤ አንድም፡ ተሐንፁ፡ ወኢትነብሩ፡ ውስቴቱ፤ ጌጠኛ፡ ቤት፡ ትሠራላችሁ፤ በዚያ፡ አትኖሩበትም፤

ወትተክሉ፡ ወይነ፡ ወኢትሰትይዎ፡ ለወይንክሙ፤

ያማረ፡ ወይን፡ ትተክላላችሁ፡ አትጠጡትም፤

፲፪፤ እስመ፡ ርኢኩ፡ ብዙኃ፡ ኃጢአተክሙ፡ ወዓቢየ፡ ጌጋየክሙ፤

ጽኑ፡ በደላችሁን፤ ብዙ፡ ኃጢ አታችሁን፡ አይቻለሁና፤

ተኃይድዎ፡ ለጻድቅ፡ ወትነሥኡ፡ ቤዛ፤

በደሉ፡ ይህ፡ ነው፤ ድኃውን፡ ትቀሙታላችሁ፡ መማለጃ፡ ትቀ በሉታላችሁ፤

ወታቴክልዎ፡ ለነዳይ፡ በውስተ፡ ኖኅት፤

ድሀውን፡ በአደባባይ፡ ታዳ ፉታላችሁ፤

፲፫፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ጠቢብኒ፡ ያረምም፡ ይእተ፡ አሚረ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ብልህ፡ ሰው፡ ዝም፡ ይላል፤ ዳኛ፡ ሲገኝ፡ ተናገር፤ ውሀ፡ ሲጐድል፡ ተሻገር፡ እንዲሉ፤

እስመ፡ እኩይ፡ መዋዕሊሁ፤

ዘመኑ፡ክፉ፡ነውና፤ አንድም፡ ተሐይድዎ፡ ለጻድቅ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ጻድቅ፡ ወልደ፡ እግ ዚአብሔርን፡ ትሰቅሉታላችሁ፤ ዋጋ፡ ትቀበሉበታላችሁ፤ ጴጥ ሮስን፡ በአደባባይ፡ ታዳፉታላ ችሁ፤ ስለዚህ፡ ነገር፡ ዮሐንስ፡ ዝም፡ ይላል፤ አንድም፡ ጌታ፡ ዓርባ፤ ዘመን፡ ይታገሣል፤ ዕለተ፡ ዓርብ፤ አንድም፡ ዓር ባው፡ ዘመን፡ ክፉ፡ ነውና፤

፲፬፤ ኅሡ፡ ሠናየ፡ ወአኮ፡ እኩየ፡ ከመ፡ ትሕየዉ፤

በሕይወት፡ ትኖሩ፡ ዘንድ፡ ክፉ፡ ያይደለ፡ በጐውን፡ ውደዱ፤

ወይሄሉ፡ እግዚአብሔር፡ ምስሌክሙ፡ ዘኮሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በረድኤት፡ ከናንተ፡ ጋር፡ ይኖራል፤

፲፭፤ እመሰ፡ ትቤሉ፡ ጸላዕነ፡ እኩየ፡ ወአፍቀርነ፡ ሠናየ፤

ክፉውን፡ ጠላን፡ በጐውን፡ ወደ ድን፡ ትሉ፡ እንደሆነ፤

አግብዑ፡ ፍትሐ፡ በኀበ፡ አንቀጽ፡ ከመ፡ ይሣሃልክሙ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮሎ፡ ይመልክ፡ ለተረፈ፡ ዮሴፍ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀ ራችሁ፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ ይቅር፡ ይላችሁ፡ ዘንድ፡ በአደባባይ፡ እውነት፡ ፍርድን፡ ፍረዱ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ውስተ፡ ኵሉ፡ መርህብ፡ ብካይ፡

በአደባባዩ፡ሁሉ፡ ለቅሶ፡ይሰማል፤

ወውስተ፡ ኵሉ፡ ፍኖት፡ ዓውያት፤

በየጎዳናው፡ ሁሉ፡ ጩኸት፡ ይሆናል፤

ወይላሁ፡ ሐረሳዊ፡ ወይበኪ፤

አራሹም፡ ያዝናል፤ ያለቅሳል፤

፲፯፤ ወእለሂ፡ የአምሩ፡ ሰቆቃወ፡ ይበክዩ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ ፍኖት፤

ሙሾውን፡ የሚያውቁ፡ ሰዎች፡ በየጐዳናው፡ ያለቅሳሉ፤

እስመ፡ የኃልፍ፡ ሞት፡ እንተ፡ ማዕከሌኪ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ሞት፡ ስልምና ሶር፡ በመካከልሽ፡ ይመጣል፡ ብሏልና፤

፲፰፤ አሌ፡ ሎሙ፡ ለእለ፡ ይፈትውዋ፡ ለዕለተ፡ እግዚአብሔር፤

ዕለተ፡ ጌዋዌን፡ ለሚወዷት፡ ሰዎች፡ ወዮላቸው፤

አኮኑ፡ ጽልመት፡ ይእቲ፡ ወኢኮነት፡ ብርሃን፤

መከራ፡ ናትና፡ ተድላ፡ ደስታ፡ አይደለችምና፤

፲፱፤ ከመ፡ ሶበ፡ ይጐይይ፡ ሰብእ፡ እምአንበሳ፡ ወይረክቦ፡ ድብ፤

ሰው፡ ከአንበሳ፡ ሸሽቶ፡ በሄደ፡ ጊዜ፡ ድብ፡ እንዲያገኘው፤

ወይበውዕ፡ ቤተ፡ ወያሰምክ፡ በዓረፍቱ፤

ከቤት፡ ገብቶ፡ ግርግዳውን፡ በተጠጋ፡ ጊዜ፤

ወይነስኮ፡ አርዌ፡ ምድር፤

እባብ፡ እንዲነድፈው፤

፳፤ ከማሁኬ፡ ጽልመት፡ ይእቲ፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፤

ይህ፡ በዚያ፡ ሰው ጭንቅ፡ እን ደሆነበት፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፡ ጌዋዌ፡ ጨለማ፡ ናትና፡ ለምን፡ ይወዷታል፤ አንድም፡ አሌ፡ ሎሙ፡ ለእለ፡ ይፈትውዋ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ጌዋዌን፡ ለሚመኟት፡ ሰዎች፡ ወዮላቸው፤ ተድላ፡ ደስታ፡ ያይደለች፡ ጨለማ፡ ናትና፡ ለምን፡ ይወዷታል? ከፋሃ፡ የቀረውን፡ ቴልጌል፤ ከቴልጌል፡ የቀረውን፡ በስልም ናሶር፤ ከስልምናሶር፡ የቀረውን፡ በናቡከደነፆር፡ አጠፋዋለሁ፤ ዕለተ፡ ጌዋዌ፡ አሁን፡ እን ደተናገርኋት፡ ናት፤

ወኢኮነት፡ ብርሃን፤

ተድላ፡ ደስታ፡ አይደለችም፤

ወቆባር፡ ይእቲ፡ ወአልባ፡ ፀዳል፤

ጨለማ፡ ናት፡ ብርሃን፡ ተድላ፡ ደስታ፡ የላትም፤

፳፩፤ ጸላዕኩ፡ ወአርኃቁ፡ በዓላቲክሙ፤

በዓለ፡ ሠዊትን፡ በዓለ፡ መጸ ለትን፡ ፈጽሜ፡ ጠላሁ፤



ወኢያዌኑ፡ መዓዛ፡ መሥዋዕቲክሙ፤

የመሥዋዕታችሁን፡ መዓዛ፡ አልቀበልም፤

፳፪፤ እመኒ፡ አምጻእክሙ፡ ሊተ፡ መሥዋዕተክሙ፡ ወቍርባንክሙ፡ ኢይ ትሜጠዎ፡ ለክሙ፤

መሥዋዕቱን፡ ቍርባኑንም፡ ብታ መጡ፡ ወድጄ፡ አልቀበለውም፤

ወኢይኔጽር፡ ለክሙ፡ መሥዋዕተ፡ መድኃኒትክሙ፤

እንድንበታለን፡ የምትሉትን፡ መሥዋዕት፡ በዓይነ፡ ምሕረት፡ አልመለከተውም፤

፳፫፤ አርኅቁ፡ እምኔየ፡ ቃለ፡ ማኅ ሌትክሙ፤

የዘፈኑን፡ ዜማ፡ ከኔ፡ አርቁ፤ አንድም፡ አርኃቁ፡ እምኔየ፡ ይላል፤ የዘፈኑን፡ ዜማ፡ ከኔ፡ አራቅሁ፤

ወኢያፀምዕ፡ መዝሙረ፡ መሰንቆክሙ፤

ዜማ፡ መሰንቆክሙ፡ ሲል፡ ነው፤ የመሰንቆዋችሁን፡ ዜማ፡ አል ሰማም፤ አንድም፡ ኢያፅምዕ፡ አልስማ፤

፳፬፤ ወየኃዝ፡ ፍትሕ፡ ከመ፡ ማይ፤

ይስማንስ፡ ካላችሁ፡ ፍርድ፡ እንደ፡ ውሀ፡ በዝቶ፡ ይፍሰስ፤

ወጽድቅኒ፡ ከመ፡ ውኂዝ፡ በድው፤

እውነተኛ፡ ፍርድ፡ እንደ፡ ምድ ረበዳ፡ ውሀ፡ ይብዛ፤

፳፭፤ ቦኑ፡ ዘአባዕክሙ፡ ሊተ፡ መሥዋዕተ፡ ወቍርባነ፡ ፵፡ ዓመተ፡ በገዳም፡ ኦ፡ ቤተ፡ እስራኤል፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

የእስራኤል፡ ወገኖች፡ አርባ፡ ዘመን፡ በምድረ፡ በዳ፡ ስትኖሩ፡ መሥዋዕቱን፡ ቍርባኑን፡ ያቀ ረባችሁልኝ፡ ማቅረብ፡ አለ?

፳፮፤ ወነሣእክሙ፡ ደብተራ፡ ሞሎህ፡ ወኮከበ፡ አምለክሙ፡ ዘስሙ፡ ሬፋን፤

አላ፡ ያለበት፡ ነው፤ እኔን፡ ጠል ታችሁ፡ ዙሐልን፡ መሸሪትን፡ አመለካችሁ፡ እንጂ፤

ዘገበርክሙ፡ በአርኢያሆሙ፡ ለአሞሬዎን፤

በአሕዛብ፡ አምሳል፡ የሠራችሁ ትን፡ጣዖት፡አመለካችሁ፡እንጂ፤

፳፯፤ ወአፍለስክሙ፡ ርኅቀ፡ እም ደማስቆ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ከኢየሩሳሌም፡ ሩቅ፡ ከሆነ፡ ከደ ማስቆ፡ ጣዖቱን፡ አመጣችሁ፤ አንድም፡ አፈልስክሙ፡ ርኁቀ፡ እምደማስቆ፤ ከደማስቆ፡ ሩቅ፡ ከሆነች፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደባ ቢሎን፡ አስማርኬ፡ እሰዳችኋለሁ።

## ምዕራፍ ፮

### ጉባኤ

፩፤ አሌ፡ ሎሙ፡ ለእለ፡ ይሜንንዋ፡ ለጽዮን፤

ጽዮን፡ ኢየሩሳሌምን፡ ለሚን ቋት፡ ሰዎች፡ ወዮላቸው፤ አን ድም፡ ሕግን፡ ለሚንቋት፡ ወዮላቸው፤

ወለእለ፡ ይትአመኑ፡ በደብረ፡ ሰማርያ፤

በሰማርያ፡ ባለ፡ ጣዖት፤ አን ድም፡ በአምባው፡ ለሚታመኑ፡ ወዮላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

ቀሰምዎሙ፡ መላእክተ፡ አሕዛብ።

የአሕዛብ፡ አለቆች፡ ማረኳቸው፤

ሖሩ፡ ቤተ፡ እስራኤል፡ ወባው፡ ውስተ፡ ካሌና፡ ከመ፡ ትርአዩ፡ ዕደው፡ እለ፡ ሀለዉ፡ ውስቴታ።

በውስጧ፡ ያሉ፡ አርበኞችን፡ ታዩ፡ ዘንድ፡ ቤተ፡ እስራኤል፡ ወደካሌና፡ ሄዳችሁ፡ ግቡ። ሰና ክሬም፡ ሠላሳ፡ ሦስት፡ ነገሥ ታት፡ በካሌና፡ አሥሮ፡ አግዞ፡ ነበርና፤

፪፤ ወርእዩ፡ ወኅልፉ፡ ኤማተርቦ።

ወደኤማተርቦም፡ ሄዳችሁ፡እዩ፤

ወረዱ፡ ውስተ፡ ጌት፡ ዘኢሎፍሊ።

የኢሎፍሊ፡ ክፍል፡ ወደምት ሆን፡ ወደጌትም፡ ሂዱ፤

ዘይጸንዑ፡ እምኵሉ፡ ነገሥት።

ከነገሥታቱ፡ ሁሉ፡ እነዚያ፡ ይጸኑ፡ ነበርና፡ እስኪ፡ እነዚ ያን፡ እዩዋቸው፤

እስመ፡ ዘይበዝኅ፡ ብሔር፡ ደወለ፡ ዚአሆሙ፡ ውእቱ።

ግዛታችው፡ ብዙ፡ ሀገር፡ ነበርና፡ እስኪ፡ እነዚያን፡ እዩዋቸው፤

፫፤ እሌ፡ ሎሙ፡ ለእለ፡ ይትሜነ ይዋ፡ ለዕለት፡ እኪት።

ዕለተ፡ ዔዋዌን፡ ለሚመኟት፡ ወዮላቸው፤

ወለእለ፡ ያስተቃርቡ፡ ወያስተላጽቁ፡ ሰንበታተ፡ ሐሰት።

ሐሰተኛውን፡ ሱባዔ፡ ለሚያቀ ራርቡ፡ ሰዎች፡ ወዮላቸው፤

፬፤ እሌ፡ ሎሙ፡ ለእለ፡ ይሰክቡ፡ ውስተ፡ አራት፡ ዘቀርን፡ ነጌ፡ ወይትፌ ግዑ፡ ውስተ፡ ምስካቦሙ።

በዝሆን፡ ጥርስ፡ አልጋ፡ ላይ፡ ተኝተው፡ ደስ፡ እያላቸው፡ ኃጢአት፡ ለሚሠሩ፡ ሰዎች፡ ወዮላቸው፤

እለ፡ ይሴስዩ፡ መሐስዓ፡ እምውስተ፡ መራዕይ።

ከብዙ፡ መንጋ፡ አንድ፡ ጠቦ ትስ፡ እንኳ፡ ቀምተው፡ ለሚ በሉ፡ ወዮላቸው፤

ወመቁዓለ፡ ላህም፡ እምውስተ፡ አዕ ፃዳተ ወፍር።

ከመሠማሪያው፡ ቦታ፡ ቀምተው፤ አንድም፡ ጾም፡ ሳይለዩ፡ የላሙን፡ ወይፈን፡ ለሚበሉ፡ ወዮላቸው፤ አንድም፡ ኃጢአት፡ ለሚሠሩ፡ ወዮላቸው፤

፭፤ እለ፡ ይጠፍሑ፡ እደ፡ ወየኀ ብሩ፡ ምስለ፡ ቃለ፡ እንዚራ።

ከበገናው፡ ዜማ፡ ጋር፡ እጃቸ ውን፡ አስማምተው፡ ለሚያጨ በጭቡ፡ ሰዎች፡ ወዮላቸው፤

ወይመስሎሙ፡ ዘኢየኃልፍ።

የማያልፍ፡ ለሚመስላቸው፤

ወኢየአምሩ፡ ከመ፡ ይመስጦሙ።

በሞት፡ እንዲወስዳቸው፡ ለማያውቁ፡ ወዮላቸው፤



፮፤ እለ፡ ይሰትዩ፡ ወይነ፡ ትዕ ግልት፡ በማሕው።

በሞ፡ ብርሌ።

ወበቢረሌ፡ ፀዓዳ።

በነጭ፡ ብርሌ፤ አንድም፡ በማ ኅው። በማለፊያው፡ ወቢረሌ፡ በተራው፡ ብርሌ፡ ቀምተው፡ ያመጡትን፡ ወይን፡ ለሚጠጡ፡ ወዮላቸው፤ አንድም፡ ያንን፡ ጠጥተው፡ ኃጢአት፡ ለሚሠሩ፡ ሰዎች፡ ወዮላቸው፤

ወይትቀብኡ፡ ዕፍረተ፡ ቅድወ።

የማረውን፡ ሽቱ፡ ለሚቀቡ፡ ማለት፡ ይህን፡ ተቀብተው፡ ኃጢአት፡ ለሚሠሩ፡ ወዮላቸው፤

ወእሙንቱ፡ የሐምሙ፡ በቀዳሚ፡ ተዴውዎ።

አሥሩ፡ ነገድ፡ ከተማረኩ፡ በኋላ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ይማረካሉ፤ አን ድም፡ በቅጥቃጤሁ፡ ለዮሴፍ፡ ይላል። አሥሩ፡ ነገድ፡ በተማ ረኩበት፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ይማ ረካሉ፤ አንድም፡ የዮሴፍን፡ መከራ፡ በሚመስል፡ መከራ፡ ይዋረዳሉ፤

፯፤ ወናሁ፡ ይእዜ፡ ዓበይቶሙ፡ ይቀድሙ፡ ተዴውዎ።

ከሁለቱ፡ ነገድ፡ አስቀድሞ፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ይማረካሉ፤ አንድም፡ [illegible] ነገደ፡

ሮቤል፡ ይማረካሉ፤ አንድም፡ ሮቤል፡ በኵር፡ ነው፤ እንደ፡ ሮቤል፡ ይማረካሉ፤

ወየኃልቁ አፍራስ፡ ኤፍሬም፡ ረዋዕያን።

ፈጣኖች፡ የሆኑ፡ የኤፍሬም፡ ፈረሶች፡ በቃታ፡ ያልቃሉ፤

፰፤ እስመ፡ መሐለ፡ እግዚአ ብሔር፡ በርእሱ።

ሕያው፡ አነ፡ አማንየ፡ በርእ ስየ፡ ብሏልና፤

እንዘ፡ ይብል፡ አኃሥሮ፡ ለዕበየ፡ ያዕቆብ።

የያዕቆብን፡ ገናንነቱን፡ አጠፋ ዋለሁ፡ ብሎ፤

ወጸላዕኩ፡ በሐውርቲሁ።

አገሩን፡ ጠላሁ።

ወአጠፍዕ፡ አህጉሪሁ ምስለ፡ እለ፡ ይነ ብሩ፡ ውስቴቶን።

በውስጡ፡ ከሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ አውራጃውን፡ አጠፋለሁ፡ ብሎ፡ ምሏልና፤

፱፤ ወእለሂ፡ ተርፉ፡ ፲ቱ፡ ውስተ፡ ፩ዱ፡ ቤት።

አሥር፡ ሰዎች፡ በአንድ፡ ቤት፡ ከዔዋዌ፡ ቢቀሩ፤

ይመውቱ።

በቀጠና፡ ያልቃሉ፤

፲፤ ወይነሥእዎሙ፡ ወይትሔ የልዎሙ።

ከሞት፡ የቀሩቱ፡ የሞቱትን፡ እናነሣቸዋለን፡ ይላሉ። ማን ሣት፡ ይሣናቸዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወያወጽኡ: አዕዕምቲሆሙ: እምነ: ቤት፣

ከዚያው: ከቤት: ቀብረው: ኋላ: አጥንታቸውን: አውጥ ተው: ይወስዷል፤ አንድም: ይት ኄየልዎሙ: ወይነሥእዎሙ: ተበረታትተው: የከሳ: ሰውነ ታቸውን: ያወጧቸዋል፤

ወይብሎ: ለዓቃቤ: ቤት: ቦሁ: ዘተ ርፈ: ኀቤከ፣

የናቡከደነፆር: ማራኪ: የስል ምናሶርን: ማራኪ: እንዲህ: ይለዋል፤

ከግዳይ: ከምርኮ: የቀረ: ካንተ: ዘንድ: አለን: ይለዋል፣

ወይቤሎ: አልቦ፣

የለም: ይለዋል፤

፲፩፤ ወይቤሎ: አርምምኬ: ከመ: ኢይጸውዑ: ስመ: እግዚአብሔር፣

የእግዚአብሔርን: ስም: ጠርተው: እንዳይድኑ: ዝም: በል: ይለዋል፤ አንድም: ወይ ቤሎ: ለዓቃቤ: ቤት: ብለህ: መልስ፣ ከእስራኤል: አንዱ: አንዱን: ከወራሪ: ከዘራፊ: የቀረ: ካንተ: ዘንድ: የለምን: ይለዋል፣ እሱም: የለም: ይለ ዋል፣ የፈጣሪያቸውን: ስም: ጠርተው: እንዳይድኑ: ሁነዋ ልና: ተዋቸው: ይበላቸው:

፲፪፤ እስመ: ናሁ: ይኤዝዝ: እግ ዚአብሔር፣

እግዚአብሔር: እነሆ: መዓት መቅሠፍት: ያዝዛልና፤

ወይነጽሖ: ለዓቢይ: ቤት: በድቀት፣

አሥሩን: ነገድ: በመከራ: ይጥ ላቸዋልና፤

ወለንዑስ: ቤት: በንጽሐት፣

ሁለቱንም: ነገድ: በመከራ: ይጥላቸዋል፤

፲፫፤ ያረውፁኑ: አፍራስ: ውስተ: ኰኵሕ: በሊሐት፣

በሻፎ: ደንጊያ: ላይ: ፈረስ: ይጋልባሉን፣ እንደዚህስ: ሁሉ: ሕግ: እግዚአብሔርን: ትታ ችሁ: ወደሕግ: ጣዖት: መሄድ: ይገባልን፤

ወያረምምኑ: እምአንስት፣

ሜዳ: ከመሆኑ: የተነሣ: ፈረስ: ከመጋለብ: ዝም: ይላልን፣ እኔስ: መዓት: መቅሠፍት: ከማምጣት: ዝም: እላለሁን፤ አንድም: ወኢያረምምኑ: ይላል፣ ገደል: ከመሆኑ: የተነሣ: ፈረስ: ከመጋለብ: ዝም: አይልምን፣ እናንተስ: ኃጢአት: መሥራ ትን: አትተዉምን፣ የሐውሩኑ: ማያት: መልዕልተ: እንሕስት: [illegible]



እንጂ: አሻቅቦ: ይሄዳልን፣ እና ንተስ: እኔን: ትታችሁ: ጣዖት: ማምለክ: ይገባችኋልን፤

እስመ: አንትሙ: ሜጥክሙ: ፍትሐ: ውስተ: መዓት፣

እናንተ: ተቆጥታችሁ: ፍርድ: ለውጣችኋልና፤

ወአምረርክሙ: ፍሬ: ጽድቅ፣

እውነት: ነገር: የያዘ: ድሀውን: አሳዝናችሁታልና፤

፲፬፤ አሌ: ሎሙ: ለእለ: ይትፌ ሥሑ: በነገረ: ከንቱ፣

በከንቱ: ነገር: ደስ: ለሚላቸው: ወዮላቸው፤

ወይብሉ: አኮኑ: በኃይልነ: በቈለ: ቀርንነ፣

ሥልጣናችን: በኃይላችን: የጸና: አይደለምን: ለሚሉ: ሰዎች: ወዮላቸው፤

፲፭፤ በእንተ: ዝንቱ: ናሁ: አነ: አነሥእ: አሕዛበ: ላዕሌክሙ: ቤተ: እስራኤል: እለ: ይሣቅዩክሙ፣

የእስራኤል: ወገኖች: ስለዚህ: ነገር: በናንተ: ላይ: መከራ: የሚያመጡባችሁ: አሕዛብን: አሁን: አሥነሣለሁ፤

ወአበውሖሙ: ይባዑ: እስከ: ኤማተርቦ፣

እስከ: ኤማተርቦ: ይገቡ: ዘንድ: አሰናብታቸዋለሁ፤

ወእስከ: ፈለገ: ዓረብ፣

በፀሐይ: መግቢያ: እስከ: አለው: [illegible] ዘንድ።

## ምዕራፍ ፯

፩፤ እስመ: ከመዝ: አርአየኒ: እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር: እንዲህ: ያለ: ነገር: አሣየኝ፤

ወናሁ ይመጽእ: አንበጣ: እምጽባሕ፣

ከፋርስ: ፉሃ: የሚባል: ንጉሥ: ይመጣል፤

አሐዱ: ደጎብያ: ጎግ: ንጉሥ፣

አሐዱ: ንጉሥ: ደጎ: ደጎብያ፣ ሲል: ነው፤ ብዙ: ሠራዊት: ያሉት: አንድ: ንጉሥ ይመ ጣል፤ አንድም: እንዳለ: ይሆ ናል፣ ብዙ: ጭፍራ: ያላቸው: ብዙ: ነገሥታት: ይመጣሉ፤

፪፤ ወይበልዕ: ኵሉ: ሣዕረ: ምድር: ወያኃልቁ፣

ዘሩን: ተክሉን: ያጠፋል: ብዛ ቱን: መናገር: ነው፤

ወእቤ: እግዚኦ: እግዚኦ: ተሣሃሎ፣

አቤቱ: አቤቱ: ይቅር: በለው: አልሁ፤

መኑ: ያነሥኦ: ለያዕቆብ: እስመ: ውኁድ: ውእቱ፣

ያዕቆብ: አንሷልና: ማን: ያበ ዛዋል፣ ተዋርዷልና: ማን: ያከ ብረዋል፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፤ ወነሥሐ፡ እግዚአብሔር፡ በእንተ፡ ዝንቱ፤

ሰው፡ ያለ፡ እውቀት፡ ሠርቶ፡ እንዲፀፀት፡ እግዚአብሔር፡ ያለ እውቀት፡ ሠርቶ፡ ተፀፀተ፡ ማለት፡ አይደለም፤ ስለዚህ፡ ነገር፡ እግ ዚአብሔር፡ አዘነ፤

ወዘኒ፡ ኢይመጽእ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ፍሃ፡ አይመጣም፡ አለ፤ መም ጣትስ፡ መጥቷል፤ ሽህ መከ ሊት፡ አስገብሮ፡ ተመልሷል፤

፬፤ ከመዝ፡ አርአየኒ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ አሣየኝ፤

ናሁ፡ ጸውዐ፡ እግዚአብሔር፡ በዓቢይ፡ ቃል፡ እሳተ፤

እግዚአብሔር፡ ቃሉን፡ አሰምቶ፡ ቴልጌልን፡ ጠራው፤

ወበልዓት፡ ዓቢየ፡ ቀላየ፤

ከተማውን፡ አጠፋች፤

ወበልዓት፡ መክፈልቶሙ፤

የእስራኤልን፡ ገንዘብ፡ አጠፋች፤

፭፤ ወእቤ፡ አነ፡ እንቢአከ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ እስራኤልን፡ ታጠፋቸው፡ ዘንድ፡ አገባብህ፡ አይደለም፡ አልሁ፤

መኑ፡ ያነሥኦ፡ ለያዕቆብ፡ እስመ፡ ውኁድ፡ ውእቱ፤

አንሷልና፡ ማን፡ ያበዛዋል? ተዋ ርዷልና፡ ማን፡ ያከብረዋል?

፮፤ ወነስሐ፡ እግዚአብሔር፡ በእ ንተ፡ ዝንቱ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ እግዚአብሔር፡ አዘነ፤

ወዝኒ፡ ኢይመጽእ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ቴልጌል፡ አይ መጣም፡ አለ፤ መምጣትስ፡ መጥ ቷል፤ ሰባት፡ አህጉር፡ ወግቶ፡ ተመልሷል፤

፯፤ ወከመዝ፡ አርአየኒ፡ እግዚ አብሔር፤

እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ገለጠልኝ፤

ወናሁ፡ብእሲ፡ይቀውም፡ዲበ፡አድማስ፤

ስልምናሶር፡ ወደ፡ ሰማርያ፡ ሲመጣ፡ አየሁ፤

ወውስተ፡ እዴሁ፡ አድማስ፤

በስልምናሶር፡ ሥልጣን፡ አለ፤ አንድም፡ ብእሲ፡ ይቀውም፡ ዲበ፡ አድማስ፡ ብለህ፡ መልስ፡ ጌታ፡ በስልምናሶር፡ አድሮ፡ ወደሰማ ርያ፡ ሲመጣ፡ አየሁት፤

ወውስተ፡ እዴሁ፡ አድማስ፤

ስልምናሶር፡በጌታ፡እጅ፡ተይዟል፤

፰፤ ወይቤለኒ፡ እግዚአብሔር፡ ምንተ፡ ትሬኢ፡ አሞጽ፤

እግዚአብሔር፡ አሞጽ፡ ምን፡ ታያለህ? አለኝ፤ ጠፍቶት፡ አይ ደለም...



ነው፤ አንድም፡ ለማንቃት፡ ለማትጋት፤

ወእቤ፡ አድማስ፡ እሬኢ፤

ስልምናሶር፡ ወደሰማርያ፡ ሲመጣ፡ አየዋለሁ፤ አንድም ጌታ፡ በስልምናሶር፡ አድሮ፡ ሲመጣ፡ አየዋለሁ፤

ወይቤለኒ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለኝ፤

ናሁ፡ አነ፡ እኤዝዝ፡ አድማሰ፡ ማዕከለ፡ ሕዝብየ፡ እስራኤል፤

በወገኖቼ፡ በእስራኤል፡ መ ካከል፡ ስልምናሶርን፡ አዝ ዘዋለሁ፡ አለኝ፤

ወኢይደግም፡ እንከ፡ አናሕስዮ፡ሎሙ፤

ዳግመኛ፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤

፱፤ ወይማስን፡ አውግረ፡ ዛውዕ፡

ጣዖት፡ የቆመበት፡ ኮረብታ፡ ይጠፋል፤

ወይጠፍዑ፡ ኄራቶሙ፡ ለእስራኤል፤

የእስራኤል፡ ደቦሎቻቸው፡ ይጠ ፋሉ፤ የከሐዲዎች፡ ሰዎች፡ ፍዳ፡ መጥቶባቸው፡ በጎዎች፡ ሰዎች፡ ይጠፋሉ፤ ማለት፡ ነው፤

ወአነሥእ፡ ኲናተ፡ ላዕለ፡ ቤተ፡ ኢዮ ርብአም፤

በኢዮርብዓም፡ ወገኖች፡ ላይ፡ ...

፲፤ ወለአከ፡ አሜስያስ፡ ካህነ፡ ቤቴል፡ ኀበ፡ ኢዮርብአም፡ ንጉሠ፡ እስራኤል፤

የቤቴል፡ ካህን፡ አሜስያስ፡ ከእ ስራኤል፡ ንጉሥ፡ ከኢዮርብ አም፡ ዘንድ፡ ላከ፤

እንዘ፡ ይብል ማዕሌተ፡ ይገብር፡ አሞጽ፡ ላዕሌከ በማዕከለ፡ ቤተ፡ እስራኤል፤

በእስራኤል፡ ወገኖች፡ መካከል፡ አሞጽ፡ በአንተ፡ ላይ፡ አመ ጽን፡ ያደርጋል፡ ብሎ፡ ላከ፤

ምድርኒ፡ ኢትክል፡ ፀዊሮቶ፡ ለኵሉ፡ ዘይነብብ፤

በአንተ፡ ላይ፡ የሚናገረውን፡ ነገር፡ ስንኳን፡ ሰው፡ ምድር፡ አትችለውም፤ አንድም፡ አይደ ረግም፡ እንጂ፡ የሚደረግ፡ ቢሆን፡ በአንተ፡ ይመጣል፡ የሚለውን፡ መከራ፡ ምድር፡ አትችለውም፤

፲፩፤ ወይብለከ፡ አሞጽ፡ በኲናት፡ ይመውት፡ ኢዮርብአም፤

አሞጽ፡ ኢዮርብአም፡ በጦር፡ ይሞታል፡ ይልሃል፤

ወእስራኤልኒ፡ ይፄወዉ፡ እምብሔ ሮሙ፤

እስራኤልም፡ ከሀገራቸው፡ ተማ ርከው፡ ይሄዳሉ፤

፲፪፤ ወይቤሎ፡ አሜስያስ፡ ለአሞጽ፡ ሑር፡ ወፍልስ፡ ብሔረ፡ ይሁዳ፡ ወን በር፡ ህየ፤

ነገር፡ ለማስመሰል፡ ነው፤ አሜ ስያስ፡ አሞጽን፡ ወደ፡ ይሁዳ፡ ሂድ፡ ከዚያ፡ ተቀመጥ፡ አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበህየ፡ ተነበይ፤
ከዚያ፡ አስተምር፤

፲፫፤ ወኢትትነበይ፡ በቤቴል፤
በቤቴል፡ አታስተምር፤
እስመ፡ ምሕራመ፡ ንጉሥ፡ ይእቲ፤
የንጉሥታቱ፡ መስገጃ፡ ናትና፤
ወቤተ፡ መንግሥት፡ ይእቲ፤
ቤተ፡ መንግሥትም፡ ናትና፤

፲፬፤ ወተሰጥዎ፡ አሞጽ፡ ለአሜስያስ፤
አሞጽ፡ ለአሜስያስ፡ መለሰለት፤
ወይቤሎ፡ አንሰ፡ ኢኮንኩ፡ ነቢየ፤
እኔ፡ ነቢይ፡ አይደለሁም፡ አለው፤
ወኢወልደ፡ ነቢይ፤
የነቢይ፡ ልጅም አይደለሁም፤
አላ፡ ተቃራሚ፡ በለስ፡ አነ፤
በለስን፡ የምለቅም፡ እረኛ፡ ነኝ፡ እንጂ፤ ምነው፡ በተረፈ፡ ቁርሎስ፡ ዘይሴሰይ፡ ሰግላ፡ ይለው፡ የለም? ቢሉ፡ መቼስ፡ እረኛ፡ አይደለም? ያንንም፡ ያንንም፡ ይመገባል፤ አንድም፡ አንሰ፡ ኢኮንኩ፡ ነቢየ፡ ብለህ፡ መልስ፤ እኔ፡ ነቢየ፡ ሐሰት፡ አይደለሁም፤ የነቢየ፡ ሐሰትም፡ ልጅ፡ አይደለሁ፤ እስራኤልን፡ የማስተምር፡ መምህር፡ ነኝ፡ እንጂ፤ አንድም፡ ትንቢቱን፡ ትምህርቱን፡ እንደ፡ አጥንት፡ እንደ፡ ጅማት፡ ከአባት፡ ከናቴ፡ አላገኘሁትም፡ ሲል ነው፡ እንጂ፡ ነቢይ፡ ነው፤ አንድም፡ ጌታ፡ እኔ፡ ሩቅ፡ ብእሲ፡ አይደለሁም፤ የሩቅ፡ ብእሲም፡ ልጅ፡ አይደለሁም፤ ምእመናንን የማስተምር፡ የባሕርይ፡ አምላክ፡ ነኝ፡ እንጂ፤

፲፭፤ ወነሥአኒ፡ እግዚአብሔር፤
እማዕከለ፡ አባግዕ፤
እግዚአብሔር፡ በግ፡ ከምጠብቅበት፡ ቦታ፡ ወሰደኝ፤ አለ፡ እንደ፡ ዳዊት፤
ወይቤለኒ፡ እግዚአብሔር፡ ተነበይ፡ ላዕለ፡ ሕዝብየ፡ እስራኤል፤
እግዚአብሔር፡ እስራኤልን፡ አስተምራቸው፡ አለኝ፤

፲፮፤ ወይእዜኒ፡ ስማዕ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፤
አሁንም፡ የእግዚአብሔርን፡ ነገር፡ ስማ፤
አንተ፡ ትቤ፡ ኢትትነበይ፡ ላዕለ፡ ቤተ፡ እስራኤል፤
አንተ፡ የእስራኤልን፡ ወገኖች፡ አታስተምር፡ ብለህ፡ ነበር፤
ወኢታንጥዮሙ፡ ለቤተ፡ ያዕቆብ፤
የያዕቆብን፡ ወገኖች፡ አትዘብዝባቸው፡ ብለህ፡ ነበር፤

፲፯፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤
ስለዚህ፡ ነገር፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ አለ፤
ብእሲትከኒ፡ ትዜሙ፡ በሀገርከ፤
አንተ፡ ሙተህ፡ ሚስትህ፡ በሀገርህ፡ የማይገባ፡ ሥራ፡ ትሠራለች፤



ወደቂቅከኒ፡ ወአዋልዲከኒ፡ ይወድቁ፡ በኲናት፤
ወንዶችም፡ ሴቶችም፡ ልጆችህ፡ በጦር፡ ይሞታሉ፤
ወይሰፍርዋ፡ ለምድርከ፡ በሐብል፤
ምድርህን፡ በገመድ፡ ተካፍለው፡ ይወርሷታል፤
ወአንተኒ፡ ትመውት፡ በምድር፡ ርኵስት፤
አንተም፡ የፈረስ፡ ምስል፡ በሚመለክበት፡ በፋርስ፡ ትሞታለህ፤
ወይፄወውዎሙ፡ ለእስራኤል፡ እምድሮሙ፤
እስራኤልን፡ ከሀገራቸው፡ ማርከው፡ ይወስዷቸዋል።

## ምዕራፍ ፰

፩፤ ከመዝ፡ አርአየኒ፡ እግዚአብሔር፤
እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ገለጸልኝ፤
ወናሁ፡ ሙዳየ፡ ኤረግ፤
እነሆ፡ ሰይፍ፡ ያለው፡ አፎት፤ አሳየኝ፤ ኤረግ፡ ሰይፍ፡ ሙዳይ፡ አፎት፡ ነው፤ አንድም፡ ኤረግ፡ ሙዳይ፡ ቢል፡ አፎት፡ ያለው፡ ሰይፍን፡ አሳየኝ፤ አንድም፡ ኤረግ፡ ሥልጣን፡ ሙዳይ፡ ናቡከደነፆር፡ ነው፡ ሥልጣኑ፡ እግዚአብሔር፡ ያደረበት፡ ናቡከደነፆርን፡ አየሁ፤ አንድም፡ ኤረግ፡ ሙዳይ፡ ቢል፡ በአፎት፡ ያለ፡ ሰይፍን፡ አሳየኝ፡ በናቡከደነፆር፡ [illegible] እግዚአብሔርን፡ አሳየኝ፡ እነናቡከደነፆር፡ እስራኤልን፡ ሲያጠፉ፡ አሳየኝ፤ አንድም፡ እንደሰይፉ፡ ስልምናሶር፡ ናቡከደነፆር፡ ናቸው፤ እንደ አፎቱ፡ እስራኤል፡ ናቸው፤ አንድም፡ ቈሬጽ፡ ይቈርጽ፡ ይላል፤ መቀስ፡ ግምጃውን፡ እያረፈ፡ ሲጥለው፡ ያያል፤ እንደመቀሱ፡ እነስልምናሶር፡ እነናቡከደነፆር፡ ናቸው፤ እንደ ግምጃው፡ እስራኤል፡ ናቸው፤ አንድም፡ ጸብታ፡ ጸግታ፡ የሚባል፡ አለ፡ ወይን፡ ጠባቆች፡ የወይኑን፡ ሐረግ፡ ቀብተው፡ በአዝመራ፡ መካከል፡ ያደርጉታል፤ ፍሬውን፡ እንበላለን፡ ሲሉ፡ አዕዋፍን፡ እንደሙጫ፡ ይይዛቸዋል፤ እንደ፡ ጸብታው፡ እነስልምናሶር፡ እንደ፡ አዕዋፍ፡ እስራኤል፡ ናቸው፤

፪፤ ወይቤለኒ፡ እግዚአብሔር፡ ምንተ፡ ትሬኢ፡ አሞጽ፤
እግዚአብሔር፡ አሞጽ፡ ምን፡ ታያለህ፡ አለኝ፤ ጠፍቶት፡ አይደለም፤ ለማንቃት፡ ለማትጋት፡ ነው፤
ወእቤ፡ ሙዳየ፡ ኤረግ፤
ሰይፍ፡ ያለው፡ አፎት፡ አያለሁ፡ አልሁ፤
ወይቤለኒ፡ እግዚአብሔር፡ በጽሐቶሙ፡ ማኅለቅቶሙ ለሕዝብየ፡ እስራኤል፤
እግዚአብሔር፡ የወገኖቼ፡ እስራኤል፡ ፍጻሜ፡ ጥፋታቸው፡ ደረሰባቸው፡ አለኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

ኢያናሐሲ: ሉሙ: ዳግመ፤

ዳግመኛ ይቅር: አልላቸውም፤

፫፤ ወያአወይዉ: በምኵራባቲ ሆሙ: ይእተ: አሚረ: ይቤ: እግዚ አብሔር፤

ያን: ጊዜ: እግዚአብሔር: በየ ቤታቸው: ያለቅሳሉ: አለኝ፤

እስመ: በዝኃ: አብድንቲሆሙ: ወዘይ ትነጻሕ: ውስተ: ኵሉ: በሐውርት: ወይትኃጐሉ፤

በየሀገራቸው: የወደቀ: ሬሳቸው: በዝቷልና: ይጠፋሉ፤

፬፤ ስምዑ: ዘንተ: እለ: ታግዕሩ: ነዳየ: በጽባሕ፤

ፈጥናችሁ: ድኃውን: የምታስ ጮሁ፤ አንድም· መቻያ: ሆና ችሁ: አድራችሁ: ሲነጋ: ድኃ ውን: የምታስጮሁ: እናንተ: ስሙ፤

ወትትዔገሉ: ምስኪነ: በዲበ: ምድር፤

በዚህ: ዓለም: ጦም: አዳሪ ውን: የምትቀሙት፤

፭፤ ወእለ: ትብሉ: ማእዜ: ይሠ ርቅ: ወርኅ፤

ሠርቀ: ወርኅ: መቼ: ይብ ታል: የምትሉ፤

ንምላዕ፤

ዓይነቱን፤

ወናስተማልዕ፤

ትርፋን: እንምላ: የምትሉ፤

ወማእዜ: ይከውን: ሰንበታቲነ፤

አሰተኛው: ሱባዔ: መች: ይደ ርሳል: የምትሉ፤

ወናርኁ: መዛግብቲነ፤

ጐተራችንን:እንክፈት: የምትሉ፤

ወንግበር: መስፈርተ: ንስቲተ፤

ታናሽ: ቁና: እንስፋ: የምትሉ: በታላቁ: ቁና: ተቀብለው: በታ ናሹ ለመስጠት፤

ወናዕቢ: መዳልወ: ዓመፃ፤

አነስተኛውን: ሚዛን: እናሰፋ: የምትሉ፤ በእውነተኛው: ሚዛን: ተቀብለው: በዓባይ: ሚዛን: ለመስጠት፤

፮፤ ወንቅኒ: ነዳየ: ባዕዳነ፤

ድኃውን: በገንዘባችን: እንግዛው: የምትሉ፤ አንድም: በእዴነ: ይላል፤ ድኃውን: በእጃችን: እንደ ወደድን: እናድርገው: የምትሉ፤

ወይኩነነ: ምስኪን: ዘንከይድ: ህየንተ: አሣዕኒነ፤

ድኃውን: ስለጫማችን: ፈንታ: እንደ: ጫማችን: እንርገጠው: የምትሉ፤

ወንትራባሕ: በትግብርተ: ዕክልነ፤

በትርፉ: ገንዘባችን: ረብኅ: ጥቅም: እናድርግ: የምትሉ: ሰዎች: በሉ፤



፯፤ መሐለኬ: እግዚአብሔር: በእ ንተ: ትዝኅርቱ: ለያዕቆብ፤

ያዕቆብ: ስለታበየ: እግዚአብ ሔር: ማለ፤

ከመ: ኢያኃልቅ: ተመውዖትክሙ: በእ ንተ: ኵሉ: ምግባሪክሙ፤

ስለክፉ: ሥራችሁ: ዘወትር: ድል: እንድትነሱ: ማለ፤

፰፤ ኢትትሀወክኑ: ምድር: በዝኒ፤

በዚህ: ምድር: አትታወክምን፤ አንድም: ኢትትሀወክ: በዚህ: አትታወክ፤

ወይልህዉ: ኵሎሙ: እለ: ይነብሩ: ውስቴታ፤

በውስጧ: የሚኖሩ: ሰዎች: ሁሉ: ያልቅሱ፤

ወይውኅዝ: ከመ: ፈለግ: ቀትል፤

ሰልፍ: እንደውሀ: በዝቶ: ይፈስሳል፤

ወይመልዕ: ከመ: ፈለገ: ግብፅ፤

በግብፅ: እንደሚፈስ: እንደ ዐባይ: ውሀ: ይበዛል፤

፱፤ ወይከውን: ይእተ: አሚረ: ይቤ: እግዚአብሔር: አምላክ፤

ያን: ጊዜ: እግዚአብሔር: እን ዲህ: ይሆናል: አለ፤

ወየዓርብ: ፀሐይ: ቀትረ: መዓልት፤

በአፍላ: ባለፀግነት: ሳሉ፤ አን ድም: በመከራ: ተይዘው: ሳሉ: ይጠፋሉ፤

ወይጸልም: ዲበ: ምድር: በዕለተ: ብርሃን፤

ተድላ: ደስታ: ባደረጉበት: ቀን: ይጠፋሉ፤

፲፤ ወእሬስዮ: ላሀ: ለበዓላቲክሙ፤

በዓሉ: ሠዊትን፤ በዓለ: መጸለ ትን: ኀዘን: አደርገዋለሁ፤

ወይከውነክሙ: ስቆቃወ: ኵሉ: መኃ ልይክሙ፤

ዘፈናችሁ: ሁሉ: ልቅሶ: ይሆ ንባችኋል፤

ወአቀንተክሙ: ብልባሌ: ውስተ: ሐቋክሙ፤

በወገባችሁ: ጨርቅ: አስታጥ ቃችኋለሁ፤

ወእወዲ: ብርሐተ: ውስተ: ርእሰ: ኵልክሙ፤

ትብትብ: ምንጣፍ: በመሸ ከም: በሁላችሁ: ራስ: ላይ ቡህነት: ትወጣለች፤

ወእሬስየክሙ: ከመ: ላሀ: ፍቁር፤

ወዳጅ: ለወዳጁ: እንዲያ ዝን፤ አንድም: ዳዊት: ለዮ ናታን: እንዳዘነ: እንድታ ዝኑ: አደርጋችኋለሁ፤

ወእለሂ: ምስሌክሙ: ይከውኑ: በዕ ለተ: ሕማም፤

ከናንተም: ጋራ: ያሉ: መከራ: በታዘዘበት: ቀን: ያዝናሉ፤

፲፩፤ እስመ: ናሁ: ይመጽእ: መዋዕል: ይቤ: እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር: እንዲህ: ያለ: መከራ: ይመጣል: ብሏልና፤

ወእፌኑ: ረኃበ: ውስተ: ምድር፤

በሀገሩ: ቀጠና: አመጣለሁ: አለ፤

www.ethiopianorthodox.org

አኮ፡ ረኃበ፡ እክል፡ ወአኮ፡ ጽምዓ፡ ማይ፤

ይኸውም፡ ከእህል፡ መራብ፡ ከውሀ መጠማት፡ አይደለም፤

ረኃበሰ፡ እምሰሚዓ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፤

ረኃብ፡ ያለውስ፡ ቃለ፡ እግዚ አብሔር፡ ከመስማት፡ መራብ፡ ነው፤

፲፪፤ ወይትሐመግ፡ ማየ፡ ባሕር፤

ሠራዊቱ ትምህርት፡ አጥተው፡ ይጠፋሉ፤

ወይረውፁ፡ እምደቡብ፡ እስከ፡ ጽባሕ፡ ይኅሥሡ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፤

እምጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፡ ሲል፡ ነው፤ እንማራለን፡ ብለው፡ ከጽ ንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፤ ከምሥ ራቅ፡ እስከ ምዕራብ፡ ይሄዳሉ፤

ወኢይረክቡ፤

ትምህርቱን፡ አያገኙም፤

፲፫፤ ይእተ፡ አሚረ፡ ይጠፍኣ፡ ደናግል፡ ላሀያት፤

ልሁያት፡ ሲል ነው፤ መልከ፡ መልካሞች፡ ቆነጃጅት፡ ትምህ ርት፡ አጥተው፡ ይጠፋሉ፤

ወይጠፍኡ፡ ሠናያን፡ ወራዙት፡ በጽምዕ፤

መልካቸው፡ ያማረ፡ ጐልማሶ ችም፡ ትምህርት፡ አጥተው፡ ይጠፋሉ፤

፲፬፤ እለ፡ ይምሕሉ፡ በምስሀለ፡ ሰማርያ፤

በሰማርያ፡ ጣዖት፡ የሚምሉ፤

እንዘ፡ ይብሉ፡ ሕይወተ፡ አምላከ፡ ዳን፤

የዳን፡ ፈጣሪ፡ ሕያው፡ ነው፡ እያሉ፤

ወሕይወተ፡ አምላከ፡ ቤርሳቤህ፤

የቤርሳቤኅ፡ አምላክ፡ በረከት ህን፡ እያሉ፡ የሚምሉ፤ አንድም፡ ሕይወተ፡ አምላከ፡ ዳን፡ ሕይ ወተ፡ አምላከ፡ ቤርሳቤህ፡ እያሉ፤

ይወድቁ፡ ወኢይትነሥኡ፡ እንከ፤

በመከራ፡ ይወድቃሉ፤ እንግዲህ በረድኤት፡ አይነሡም።

## ምዕራፍ ፱

፩፤ ርኢክዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ይቀ ውም፡ ዲበ፡ ምሥዋዕ፤

እግዚአብሔርን፡ በመመስገ ኛው፡ ቦታ፡ ሆኖ፡ አየሁት፤

ወይቤለኒ፡ ዝብጥ ፩ተ፡ አዕማደ፡ ጽጌ ያት፡ ወያድለቀልቁ፡ ዴዴያት፤

በለዝንና፡ ያቁምን፡ ገፍተህ፡ ጣላ ቸው፤ ደጆች፡ ሁሉ፡ ይነዋወጡ አለኝ፤ አንድም፡ ንጉሡ፡ ሊቀ፡ ካህናቱ፡ ይጥፉ፤ በንጉሡ፡ በሊቀ፡ ካህናቱ፡ የጸኑ፡ ሁሉ ይጥፉ፡ አለኝ፤

እስመ፡ እቀትሎሙ፡ በኵናት፤

በጦር፡ አጠፋቸዋለሁና፤

ወይመትርዎሙ፡ አርእስቲሆሙ፤

ቸብቸቢቸውን፡ ይቆርጧቸዋል፤

ወአልቦ፡ ዘያመስጥ፡ እምእለ፡ ተርፉ፤

ከቀሩት፡ ሰዎች፡ ከሞት፡ የሚያ መልጥ፡ የለም፤

ወአልቦ፡ ዘይድኅን፡ እምኔሆሙ፤

ከነዚያ፡ ወገን፡ የሚድን፡ የለም፤



፪፤ ወእመኒ፡ ወረዱ፡ ውስተ፡ ቀላይ፡ እምህየኒ፡ እደየ፡ ታወጽኦሙ፤

ወደወንዝም፡ ቢወርዱ፡ ሥል ጣኔ፡ ከዚያ ታወጣቸዋለች፤

ወእመኒ፡ ዓርጉ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ እም ህየኒ፡ ያጸድፎሙ፤

ወደ፡ አምባውም፡ ቢወጡ፡ ከዚ ያም፡ አወርዳቸዋለሁ፤

፫፤ ወእመኒ፡ ተኀብኡ፡ ውስተ፡ ቀርሜሎስ፡ በህየኒ፡ እትኃሠሦሙ፡ ወአወጽኦሙ፤

በዱርም፡ ቢሠወሩ፡ ከዚያ፡ ተመራምሬ፡ አወጣቸዋለሁ፤

እመኒ፡ ተሰጥሙ፡ ውስተ፡ ቀላየ፡ ባሕር፡ እምቅድመ፡ አዕይንትየ፡ እኤዝዞ፡ ለከይሲ፡ ወይቀስጽዎሙ፤

ከፊቴ፡ የተሠወሩን፡ መስሏቸው፡ እነኪራም፡ ከባሕር፡ ቢገቡ፡ ናቡ ከደነየርን፡ አዝዘዋለሁ፤ ይውጣ ቸዋል፡ ማለት፡ ያጠፋቸዋል፤

፬፤ ወእመኒ፡ ዔወውዎሙ፡ ፀሮሙ፡ እምቅድመ፡ ገጽየ፡ በህየኒ፡ እኤዝዛ፡ ለኵናት፡ ወትቀትሎሙ፤

ከገጸ፡ መዓቴ፡ የተነሣ፡ ጠላ ቶቻቸውም፡ ቢማርኳቸው፡ በዚ ያም፡ ጦር፡ አዝዛለሁ፡ ታጠ ፋቸዋለች፤

ወአወትር፡ አዕይንትየ፡ ላዕሌሆሙ፡ በእ ኩይ፡ ወአኮ፡ በሠናይ፤

በበጎ፡ ያይደለ፡ በክፉ፡ አስተ ያየት፡ አትኩሬ፡ አያቸዋለሁ፤

፭፤ ወይቤ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ዘይገሥሣ፡ ለኵላ፡ ምድር፡ ወያንቀለቅላ፤

ይችን፡ ዓለም፡ በመዓት፡ የሚ ዳስሳት፡ የሚያነዋውጣት፡ እግ ዚአብሔር፡ እንዲህ አለ፤

ወይላህዉ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይነብርዋ፤

በዚህ፡ ዓለም፡ የሚኖሩ፡ ሁሉ፡ ያዝናሉ፤

ወይውኅዝ፡ ከመ፡ ፈለግ፡ ቀትል፤

ስልፍ፡ እንደፈሳሽ፡ ውሀ፡ በዝቶ፡ ይደረጋል፤

ወይወርድ፡ ከመ፡ ፈለገ፡ ግብጽ፤

ግብፅን፡ እንደሚያጠጣ፡ እንደ፡ ዓባይ፡ ውሃ፡ ይበዛል፤

፮፤ ዘየሐንፅ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ ጽርሖ፤

አዳራሹ፡ ጠፈርን፡ በሰማይ፡ የሚ ያጠናው፡ እርሱ፡ ነው፤

ወይሣርር፡ ውስተ፡ ምድር፡ ትእዛዞ፤

ትእዛዙንም፡ በዚህ፡ ዓለም፡ የሚ ያጸና፡ እሱ፡ ነው፤

ዘይጼውዖ፡ ለማየ፡ ባሕር፡ ወይክዕዎ፡ ውስተ፡ ገጸ፡ ለምድር፤

ውቅያኖስን፡ በደመና፡ ቋጥሮ፡ በነፋስ፡ ጭኖ፡ የሚያመጣው፡ በዚህ፡ ዓለም፡ የሚያዘንበው፡ እሱ፡ ነው፤ አንድም፡ ስልምና ሶርን፡ ጠርቶ፡ የሚያመጣው፡ በኢየሩሳሌም፡ የሚያሰፍረው፡ እርሱ፡ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ያቀናሉ፣ ወይነብሩ፡ ውስቴታ፡

ተሐንፁ፡ ቤተ፡ ወኢትነብሩ፡ ብሎ፡ ነበርና፡ በኢየሩሳሌም፡ ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ ተዘልሎ ሰው፡ ይኖራሉ፤

ወይተክሉ፡ ወይነ፡ ወይሰትዩ፡ ወይኖሙ፣

ትተክሉ፡ ወይነ፡ ወኢትሰትዩ፡ ብሎ፡ ነበርና፣ ወይኑን፡ ይተክላሉ፣ ይጠጣሉ፣

ወይተክሉ፡ አዕፃዳተ፡ አቅማሕ፡ ወይበልዑ፡ ፍሬሁ፣

ተክል፡ በሚተክሉበት፡ ቦታ፡ ሁሉ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ተክል፡ ይተክላሉ፣ ፍሬውን፡ ይበላሉ፤

፲፭፤ ወእተክሎሙ፡ ውስተ፡ ምድሮሙ፣

በሀገራቸው፡ አጸናቸዋለሁ፤

ወአልቦ፡ እንከ፡ ዘያወጽኦሙ፡ እምድሮሙ፡ እንተ፡ ወሀብክዎሙ፡ አነ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እኔ፡ ከሰጠኋቸው፡ አገር፡ የሚያስወጣቸው፡ የለም አለ፤

ተፈጸመ፡ ዘአሞጽ፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ ትኩን፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፣

ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፡ አሜን፡፡

# ዘሚክያስ ነቢይ

## መቅድም

ሚክያስ፡ ማለት፡ መኑ፡ ከማከ፡ መኑ፡ ከመ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው፤ ትውልዱ፡ ከነገደ፡ ብንያም፡ ነው፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ሚክያስ፡ ነቢይ፡ ወልደ፡ ሞራት፣

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ ከሞራት፡ ልጅ፡ ከሚክያስ፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤

በመዋዕለ፡ ያዚያን፡ ወኢዮአታም፡ ወአካዝ፡ ወሕዝቅያስ፡ ነገሥተ፡ ይሁዳ፣

እለ፡ ነግሡ፡ በይሁዳ፣ እለ፡ ነግሡ፡ ለይሁዳ፡ ይላል፣ በይሁዳ፡ በነገሡ፡ በነዚህ፡ ዘመን፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ ስለ ምን፡ እነዚህን፡ አነሣቸው፡ ቢሉ፣ በነዚህ፡ ዘመን፡ ብመክራቸው፡ ባስተምራቸው፡ አንሰማም፡ ብለው፡ ጠፉ፡ ለማለት፤

ዘርእየ፡ በእንተ፡ ሰማርያ፣

ሰማርያ፡ እንድትጠፋ፡ ዓይቶ፤

ወበእንተ፡ ኢየሩሳሌም፣

ኢየሩሳሌምም፡ እንድትጠፋ፡ ዓይቶ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ እንዲማረኩ፡ ዓይቶ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ ነው፤

፪፤ ስምዑ፡ አሕዛብ፣

አሕዛብ፡ ስሙ፤

ወታዕምዕ፡ ምድር፣

ምድርም፡ ትስማ፡ ማለት፡ የተከሉባትን፡ አታጽድቅ፡ የዘሩባትን፡ አታብቅል፤

ወኵሎሙ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስቴታ፣

በውስጧ የሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይስሙ፤

ወይከውነክሙ፡ እግዚአብሔር፡ ሰማዕተክሙ፣

አንሰማም፡ ብትሉ፡ እግዚአብሔር፡ ምስክር፡ ይሆንባችኋል፤

www.ethiopianorthodox.org